
# ገድለ ማርያም መግደላዊት

## በአማርኛ




በአሥራ ሁለቱ ወራት የሚነበብ
ለጸሎት እጅግ ጠቃሚ የሆን

፳፲፩ ዓ.ም

Scanned with CamScanner

# ገድለ ማርያም መግደላዊት

## በአማርኛ

በአሥራ ሁለቱ ወራት የሚነበብ

ለጸሎት እጅግ ጠቃሚ የሆነ።

አሳታሚ እና አከፋፋይ

የኮተቤ ሀገረ ገነት ቅ/ጊዮርጊስ እና

ቅ/ማርያም መግደላዊት ቤተክርስቲያን

ያለ አሳታሚው ፈቃድ ማባዛትም ሆነ

መልሶ ማሳተም በሕግ ያስቀጣል

© መብቱ የባለቤቱ ነው

Scanned with CamScanner

# ገድለ ማርያም መግደላዊት ሰማዕተ ክርስቶስ
# የክርስቶስ ምስክር የማርያም መግደላዊት ገድል
## ምዕራፍ አንድ

አንድ አምላክ በሆነ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም የቅድስት ማርያም መግደላዊትን ገድሏን ምስጋናዋን ልዕልናዋንና ክብሯን እንጽፋለን።

፩. የማርያም መግደላዊት የቅደስናዋን ገናንነት በዕዝነ ልቡናው ለሚሰማው በዓይነ ሕሊናውም ለሚያየው ደስ የሚያሰኘው ዕፁብ ድንቅ ነው።

፪. የቅድስት ማርያም መግደላዊት ከሁሉ አስቀድሞ በልደቷ ዕለት ጥር ፲ ቀን የሚነበብ የገድሏ ነገር ይህ ነው። የዚህችም ቅድስት አመጣጥና ትውልዷ በወገን ከከበሩ ነገሥታት ቤተሰብ ነው።

፫. የአባቷ ስም አጤኅኖስ የእናቷ ስም ኢዮጵራቅልያ ነው። ልጅም ስለሌላቸው በቀንና በሌሊት በምሕላ እያዘኑ ይኖሩ ነበር።

፬. የእነርሱም ትውልዳቸው ከከበሩ ነገሥታት ወገን ነው። ሀገራቸውም መግዶል ነው። በሀገራቸውም ውስጥ እንደእነርሱ ታላቅና ደግ የለም ነበር። በሕገ እግዚአብሔር ጸንተው ይኖሩ ጾምና ጸሎትም ያበዙ ነበር።

፭. የአጤኅኖስም አባት ሁለት ወንዶች ሶስት ሴቶች ልጆችን ወለደ የእነርሱም በመታወቅ ስማቸው አልተጠራም የአጤኅኖስ ግን በሀገራቸው ሁሉ በመታወቅ ስሙ የሚጠራ ሆነ።

፮. አጤኅኖስም ለአቅመ አዳም ሲደርስ ከከበሩ ነገሥታት ወገን ያማረች የተዋበች ልዕልት ብላቴና ኢዮጵራቅልያን አግብቶ



Scanned with CamScanner

በማስተዋል በመጠበቅ በፍቅር በሰላም ብዙ ዓመታትን ኖሩ።

፯. እንግዳ መቀበልን የሙት ልጅ መርዳትን ይወዱ ነበር ልባቸው እዳመለከታቸውም መልካም ሥራ እየሠሩ ከዋዛ ከፈዛዛ እርቀው ነገረ እግዚአብሔርን እየተናገሩ ከሐሰት ርቀው እውነትን እየተናገሩ በልዕልና በክብር የጸኑ ሆኑ።

፰. ከዚህም በኋላ ልጆችን ይሰጣቸው ዘንድ ወደ አምላካቸው ለመኑ ይህችም የከበረች በፈቃደ እግዚአብሔር በብሥራተ መልአክ ተሰጠቻቸው በመልካም አስተዳደግም እስከ ሰባት ዓመት ተንከባከቧት።

፱. ሰባት ዓመትም በሞላት ጊዜ በወርቅና በብር ያማረ ቤት አሠሩላት በዚያም በታነጸላት ግንብ ቤት ውስጥ ከወርቅና ከብር ጠረጴዛ አዘጋጁላት።

፲. ያስተምራትም ዘንድ የብሉይ ኪዳን መምህር ሽማግሌ ሰው አመጡላት እንዲህም አድርገው በሠሩላት ቤት ውስጥ አኖሯት እርሷን ለማገልገልም ሶስት አገልጋይ ሴቶችን ቀጠሩላት።

፲፩. ከዚህ በኋላም የሕንጻውን በር ዘጉላት ያ ሽማግሌ መምህርም በውጭ ሆኖ ያስተምራት ነበር።

፲፪. በአንዲት ዕለትም በዚያ ሕንጻ ውስጥ ሳለች በአፏ የወይራ ቅጠል የያዘች ርግብ አየች በማዕድ ላይም አስቀመጠች /አኖረችው/ ከዚህም በኋላ ንስር መጣ ከእርሱም ጋር አክሊል አለ በማዕዱ ላይም አኖረው ደግሞ ቁራ መጣ ከእርሱም ጋር ከይሲ አለ በማዕዱ ላይም አኖረው ከዚህም ራዕይ የተነሣ ደነገጠች ለመምህሯም ነገረችው።

፲፫. እርሱም እንዲህ ብሎ ተረጎመላት ርግብ የሕግ ምሳሌ /ምልክት/ ናት የዘይቱም ቅጠል የክርስትና ጥምቀት ናት

ንስርም ድል አድራጊነት ነው አክሊልም ለሰማዕታት የሚሰጥ ክብራቸው ነው ቁራ የንጉሥ ምሳሌ ነው ከይሲውም መከራ ነው አንቺም የክብር ባለቤት ስሆነ ጌታ ክርስቶስ ስለ ስሙ ትጋደዪ ዘንድ አለሽ ሲል ተረጎመላት።

፲፬. ንጉሥ አባቷም ይጎበኛት ዘንድ መጣ እንዲህም አላት ለአንድ ታላቅ መኮንን ላጋባሽ እወዳለሁ። እርሷም ከልቤ እስክመክር አባቴ ሆይ ሶስት ቀኖችን ታገሰኝ ብላ ለመነችው።

፲፭. አባቷም በሄደ ጊዜ በዚያ አዳራሽ ውስጥ በሚኖሩ ጣዖታት ዘንድ በምስላቸው ፊት ቁማ ስለጋብቻ ያማክሯት ዘንድ ለመነቻቸው ከቶ አልተናገሯትም አንድ ቃልም አልመለሱላትም።

፲፮. የከበረች ማርያም መግደላዊት ግን ዓይኖቿን ወደ ሰማይ አቅንታ የክርስቲያን አምላክ ሆይ ወደምትፈቅደው መንገድ ምራኝ ብላ ጸለየች በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ መጥቶ አይዞሽ አትፍሪ የክርስቶስ ሙሽራ ነሽ ብሎ አጽናንቷት ከእርሷ ተሰወረ።

፲፯. ከዚህም በኋላ ቆማ ጸለየች ብርሃናውያን መላእክትም ወደ ርስዋ መጥተው በእግዚአብሔር ቤቶች በሰማያት የሚሆነውን ተድላ ደስታ ነገሩዋት።

፲፰. የንጉሥ ልጅ ማርያም መግደላዊት በአዳራሹ ውስጥ በምትኖር ጊዜ አስቀድማ ያደረገችውን እንነግራችሁ ዘንድ ዳግመኛ ስሙ ጣዖቱን የሚያመልኩ ሰዎች ሲያጥኑ ወላጆቿ ልማዳቸውን እንዳስተማሯት ከእርሳቸው ጋር ታጥን ነበር።

፲፱. ወደ እግዚአብሔር ከተመለሰችበት ዕለት ወዲህ ግን የመንግሥተ ሰማያትን መንገድ ይመራት ዘንድ ፊቷን ወደ



Scanned with CamScanner

ምሥራቅ መልሳ ለመነች መንፈስ ቅዱስ የአንድነቱንና የሶስትነቱን ምስጢር አስተማራት።

፳. ከዚህም በኋላ ንጉሥ አባቷ ወደርሷ መጥቶ ልጅ እንደምን አለሽ? አላት የክብር ባለቤት በሆነ በክርስቶስ ሕይወት አለሁ አለችው አባቷም እጅግ ደንግጦ ልብሽን ምን ለወጠው አላት እርሷም ሰማይና ምድርን ከፈጠረ አምላክ ተማርሁ አለችው እርሱም እያዘነ ሄደ።

፳፩. በዚህን ጊዜም የከበረች ማርያም መግደላዊት ተነሥታ ወደ እግዚአብሔር ጸለየች ወዲያውኑ የእግዚአብሔር መልአክ ወደርሷ መጥቶ እንዲህ አላት እድል ፈንታሽ ከቅዱሳን ጋር ሆኖ በጎ ዋጋን ታገኚ ዘንድ አለሽና ጽኚ በርቺ ከንጉሥ አባትሽና ከሶስት ነገሥታት ዘንድ ትሠቃያለሽና።

፳፪. ከዚያም በኋላ ሥጋውና ደሙን እስከምትቀበልና እስከምትጠመቅ ድረስ ከመላእክት አንዱ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል አምሳል አተማት ያን ጊዜም ወደ ጣዖታቱ ቤት ገብታ አተኩራ ተመለከተቻቸውና ምስሉን ሰበረች የመቀመጫውን መሠረትም አፈራረሰች።

፳፫. ንጉሥ አባቷም አይቶ እጅግ ተቆጣ ሰቅለውም እንዲገርፏት አዘዘ ከሥጋዋም በደም ፈንታ ማር ወጣ።

፳፬. ዳግመኛም በብረት አልጋ ላይ አስተኝተው ከበደታቿ እሳትን አነደዱ እርሷን ምንም አልነካትም ነገር ግን ያ እሳት ከአረማውያን መቶ ሺህ አቃጠለ።

፳፭ ከዚህም በኋላ ከብረት አልጋ ጋር ወደ ባሕር እንዲጥሉዋት አዘዘ በጸለየችም ጊዜ የክብር ባለቤት እግዚአብሔር ወደርሷ መጥቶ በህይወት ውሃ አጠባት መልአኩ ፋኑኤልም ሕብስት ሰማያዊ መገባት ከጣዖታት ርኩሰትም አነጻት በምስክርነት ያፈሰሰችው ደሟም በሽተኞችን የሚፈውስ ሆነ ሰማይና ምድርን በፈጠረ አምላክ ላይ ሰውነቷን ስለጣለች

ለእግዚአብሔር የተመረጠች ለሰማያዊ መንግሥትም የተጠራች ሆናለች።

፳፮. ዳግመኛም ስሙ ድዲዮስ የሚባል ሌላ መኮንን መጣ የከበረች ማርያም መግደላዊትንም ያመጧት ዘንድ አዘዘ የከበረች ማርያም መግደላዊትንም ያመጧት ዘንድ አዘዘ ሰቅለውም እንዲገርፏት ከበታቿም እሳትን እንዲያነዱባት አደረገ የተከተሏትም ሴቶች ባዩ ጊዜ መኮንኑን ረገሙት እርሱም ራሳቸውን በሰይፍ አስቆረጠ ፈጽሞ የማይጠፉ የድል አድራጊነት አክሊልን በመንግሥተ ሰማያት ተቀበሉ።

ጸሎታቸውና በረከታቸው በሁላችን ይደርብን አሜን

## ምዕራፍ ሁለት

አንድ አምላክ በሆነ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በየካቲት ወር በስድስት የሚነበብ የብፅዕት ማርያም መግደላዊት ዜና ገድሏ ይህ ነው። ልመናዋና በረከቷ ከእኛ ጋር ይሁን አሜን።

፩. ዳግመኛም ስለሃይማኖቷ አባቷ ጠየቃት እርሷም እንዲህ ብላ መለሰችለት። በከበረች ድንግል እመቤታችን ማርያም ልጅ በሆነው እርሱም ሕያው ነው ሰማይና ምድርን በፈጠረ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የማምን ክርስቲያን ነኝ።

፪. ይህንንም ሰምቶ አባትዋ በእርሷ ላይ ተቆጣ አስረውም በከተማው መካከል በመንገድ ላይ ጥለው በፈረሶች እንዲያስረግጧት አዘዘ ሎሌዎቹም እንዳዘዛቸው አደረጉባት ከቶ ምንም ክፉ ነገር አልደረሰባትም።

፫. እናትና አባቷም ይህን ድንቅ ሥራ ባዩ ጊዜ እጅግ አደነቁ የክብር ባለቤት በሆነ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ ምድራዊ መንግሥታቸውንም ትተው አስቀድሞ ልጃቸው ትኖርበት ወደነበረው አዳራሽ ሄደው ከዚያም ገብተው የሚኖሩ ሆኑ።



Scanned with CamScanner

፬. በሀገራቸው አቅራቢያ የሚኖር ንጉሥ፡ በእነርሱ የሆነውን ዜናቸውን በሰማ ጊዜ ወደዚያች ሀገር መጥቶ ለምን መንግሥታችሁን ተዋችሁ አሁንም ወደ መንግሥታችሁ ተመለሱ አላቸው እነርሱ ግን የዚህን ዓለም መንግሥት አንፈቅድም አሉት እርሱም መንግሥታቸውን ወስዶ በዚያች ሀገር ላይ ነገሠ።

፭. የከበረች ማርያም መግደላዊትንም ይዞ አሠቃያት የተራቡ አናብስትንና የሚናደፉ እባቦችን በላይዋ ላይ ሰደደ ከክፉ ነገር ከቶ ምንም አልደረሰባትም። ከዚህም በኋላ በመጋዝ መገዛት በአንገቷም ታላቅ ደንጊያ አደረገ ይህም ሥቃይዋ ወደ ክብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደረሰ ጌታችንም አዳናት።

፮. ከዚህም በኋላ ያጠምቃቸው ዘንድ እናትና አባቷ ካህን ቄስ ጠርተው ከርሳቸው ጋር ሶስት መቶ አገልጋዮቻቸው ተጠመቁ ከዘመዶቻቸውና ከሀገር ሰዎች ብዙዎች አምነው ተጠመቁ።

፯. ዳግመኛም ንጉሥ ኑማርያኖስ መጣ ዜናዋንም ሰማ ወደርሱም አስቀርቦ በክፉ አሟሟት እንዳትሞቺ ለአማልክት ሰዊ አላት እርሷም የክብር ባለቤት በሆነ በጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ታምኛለሁ እኔ አልሞትም አለችው። ቀላኒካ ወደሚባል ሀገር ወሰዳትና በዚያ ጽኑ የሆነ ሥቃይን አሠቃያት ከነሐስና ከብረት በበሬ አምሳል ከተሠራ ቀፎ ውስጥ አስገብቶ አሰራት።

፰. እግዚብሔርም ያንን ከነሐስ የተሠራውን ቀፎ ሰብሮ ከውስጡ አወጣት።

፱. ንጉሥ ኑማርያኖስም ሙቶ በእርሱ ፈንታ ሳቦር ነገሠ የቅድስት ማርያም መግደላዊትንም ዜናዋን በሰማ ጊዜ

ከተአምራቷ የተነሣ አደነቀ እንዲህም አላት ልጄ ሆይ በክፉ አሟሟት እንዳትሞቺ የምነግርሽን ሰምተሽ ለአማልክቶቹ ሠዊ እርሷም ለንጉሡ እንዲህ አለችው እኔስ የክብር ባለቤት ከሆነ ከጌታዬ እግዚአብሔር በቀር ለሌላ አምላክ አልሰግድም አልሠዋምም ወደ እግዚአብሔርም ምሕረትን ርዳታን ለመነች ጩኸቷ ልመናዋ ወደ አርያም ደርሶ ተሰማ፡፡

፲. በዚያን ጊዜም በእጁ ውስጥ ባለ ጦር ወጋትና ሞተች እግዚአብሔርም ከሞት አስነሳትና ያለምንም ጥፋት ጤነኛ ሆነች፡፡

፲፩. ንጉሥ ሳበርም ይህን ድንቅ ተአምር አይቶ ሰገደላት የክብር ባለቤት በሆነ በጌታችን እግዚአብሔርም አመነ፡፡ ከሀገር ሰዎችም ብዙዎች አሕዛብ ከእርሱ ጋር አመኑ ከእርሱ ጋር ያመኑትም ቁጥራቸው አሥር ዕልፍ ሶስት መቶ ሆነ

፲፪. በዚያች አዳራሽ የሚኖሩ አባትና እናቷም አረፉ፡፡

፲፫. ይቺንም የከበረች ማርያም መግደላዊት መለኮታዊት ኃይል ተሸክማ ወደ ኤፌሶን ከተማ አደረሰቻት በዚያም ድንቅ ድንቅ ተአምራትን አደረገች፡፡

፲፬. የክብር ባለቤት በሆነ በፈጣሪ እግዚአብሔር ስም በመታመን በፋርስ ንጉሥ ፊት በመቄዶንያ፣ በቀላኒካና በቁስጥንጥንያ ነገሥታት ፊት ከመሰከረች በኋላ ቤተክርስቲን ተሰራላት በጸሎቷም ኃይል በዚያች ሀገር ውስጥ ታላቅ ተአምር ይደርጋል፡፡ ሐንካሶች በትክክል ይሄዳሉና ዕውራንም አይተዋልና ደንቆሮዎች ሰምተዋልና ዲዳዎችም ተናግረዋልና ለምጻሞችም ነጽተዋልና፡፡



Scanned with CamScanner

፲፫. ለእኛም ለወንዶችና ለሴቶች አገልጋዮቿ የጸሎቷ ኃይል እንደጋሻ ይሁንልን ለዘላለሙ አሜን፡፡

## ዐርኬ

መታሰርና የፈረስ እግር ሊያሳምማት ያልቻለ በጾና ሃይማኖት ቁማ በተመለከቱ ጊዜ እናትና አባትዋ ፍለጋዋን የተከተሉ የጥምቀትንም ምስጢር በሕልሟ ላየች 'ለማርያም መግደላዊት ክብር ሰላምታ ይገባል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

፩. እናታችን ሆይ በስምሽ የታነጸችውን ቤተ መቅደስሽን በጸሎትሽ ጠብቂያት ለዘላለሙ በመዓት አትመልከቻት ነገር ግን ክብሩ ሶስተኛ እንደሚሆን እንደካህኑ እንደ አልአዛር ልጅ ፊንሐስ ከጸራ ወርቅ በተሠራ በሚያስመካ በቅድስና ልብስ ሽልሚያት፡፡

፪. ለእስራኤልም ምድረ ርስትን እንደአወረሳቸው እጅንም በአነሣ ጊዜ ጠላቶች ድል እንደሆኑለት እንደነዌ ልጅ ኢያሱ፡፡

፫. በእግዚአብሔር ዘንድ እንደተወደደ ሳሙኤልም፡፡

፬. በዳዊት ዘመን ትንቢትን እንደተናገረ እንደናታን፡፡

፭. ጆግና ጎልያድን በገደለው ከእስራኤል ልጆችም ስድብን እንዳራቀ እንደ ዳዊት

፮. ምውት እንዳስነሣ እሳትንም ከሰማይ እንዳወረደ እርሱ ራሱም በሚነድ እሳትና በእሳት ፈረሶች ወደሰማይ እንደአረገ እንደ ኤልያስ፡፡

፯. በዘመኑ ጠላቶች ሊያስደነግጡት አዳልቻሉ በሕይወት ሳለ አንድ ምውት ከሞተ በኋላ አንድ ምውት እንዳስነሣ እንደ ኤልሳዕ፡፡

፰. ሀገሩን አጽንቶ እንደጠበቀ የፋርስንም ሠራዊት ገድሎ ስለጽዮን የሚያለቅሱትን ደስ እንዳሰኛቸው የኢየሩሳሌምን ርኩሰቷንና ኃጢአቷን እንዳስወገደ እንደ ሕዝቅያስ፡፡

፱. ከእናቱ ማህፀን እንደተቀደሰ እንደ ከበረ እንደኤርምያስ፡፡

፲. የእግዚአብሔር ጌትነቱን እንዳየ እንደ ሕዝቅኤል

፲፩. በክንድ ውስጥ ሆኖ ደስ እንደሚያሰኝ አሸንክታብ የሆነ እንደ ዘሩባቤል፡፡

፲፪. በቦታቸው ልጆቻቸው እንደተተኩላቸው እንደ አሥራ ሁለቱ ደቂቅ ነቢያት፡፡

፲፫. የወደቀውን ቅጽር አንሥተው እንደሠሩ ክብርንም እንዳገኙ እንደ ሆሴዕና ነህምያ፡፡

፲፬. እንደርሱ ያለ ሰው ያልተወለደ እንደ ዮሴፍ፡፡

፲፭. በክብራቸው የሚመስላቸው ሰው እንደሌለ እንደሴምና እንደ ሴት፡፡

፲፮. በፍጥረቱ ሁሉ ላይ ንጉሥ እንደሆነ እንደ አዳም፡፡

፲፯. የካህን ልጅ ስምዖንም በዘመኑ ቤተ መቅደስን እንደሠራ ይህም የእስራኤል ሕዝብ ከምርኮ በተመለሱ ጊዜ ነው፡፡

፲፰. ከእናታችን ማህፀን ካወጣን ጀምሮ እድሜያችንን የሚያስረዝም በቦታው ሁሉ ታላላቅ ተአምራትን የሚያደርግ ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠረውን አምላክ ፈጽመው አመሰገኑት፡፡

፲፱. ይህንንም በመንፈስ ቅዱስ ተናግራ ንጉሥ ሳቦርን የሕይወትን መንገድ መራችው እርሱም ይህን ሰምቶ እምነቱን አጸና ፈጽሞ በማድነቅም አንደበቱን ከፍቶ እንዲህ አለ መሪ የሆንሽ አንቺን የሰጠኝ የአባቶቼ ፈጣሪ ይመስገን አንቺ የብርሃን መሰላል ሆነሽኛልና ፡፡

፳. እኔንም ለዘላለሙ የማያልቅ የሕይወትን ሥልጣን በሰጠኝ በአምላክሽ አመንኩ አሜን

## ምዕራፍ አራት

፩. ይህችም የከበረች ማርያም መግደላዊት እንዲህ አለችው ሰማይና ምድርን በፈጠረ አምላክ ያመንክ ከሆነ እንዲህ ያለች እምነት ወደ ሕይወት አድርሳ ከጻድቃን ጋር በመንግሥተ ሰማያት ዕድል ፈንታህ ከእርሳቸው ጋር ይሆናልና፡፡ በእውነት እመን አለችው፡፡

፪. እርሱም ይሁን እፈቅዳለሁ ብሎ መለሰላት ሁለተኛም በሀገሬ ውስጥ በስምሽ መታሰቢያ መቅደስ እንዲሠራ ከአንቺ እሻለሁ አላት፡፡

፫. እርሷም መልካም ነው ግን ከሁሉም አስቀድሞ ከሀገር ሰዎች ጋር እመኑ አለችው፡፡

፬. የከበረች ማርያም መግደላዊትም ዐይኖችዋን ወደ ሰማይ አቅንታ እንዲህ ብላ ወደ እግዚአብሔር ጸለየች አናንያ አዛርያና ሚሳኤልን በሚነድ እሳት መካከል ሆነው ሲዘምሩ በዘመናቸው የናቡከደነጾር ልቡን ወደ በጎ ሥራ አንተን ወደ ማመን የመለስክ የእኔን የባርያህን ልመና ስማኝ፡፡

፭. እኔም እንደርሳቸው እዘምርልሃለሁ በመቅደስህ አዳራሽም ውስጥ እሰግድልሃለሁ ድህነትን የምታደርግልኝ ፈጣሪዬ

ስማኝ በፍጹም ልቡናዬም ጠዋትም ማታም በዘመኔ ሁሉ እገዛልሃለሁ።

፮. እንዲሁም ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ብላ ጸለየች። የቀድሞውን አካሄዴንና ኑሮዬን አንተ ታውቃለህ የእኔን የመዳተኛ ባርያህን የማርያም መግደላዊትን ልመናዬንና ምልጃዬን ስማ።

፯. እኛንም እንደበደላችን አታጥፋን እኒህንም በዚህ ሀገር የሚኖሩትን ወንዶችና ሴቶች ባሮችህን ይቅር በላቸው ፍጥረቶችህንም አታጥፋ ሕዝብህንም ቸል አትበል የዚህችን ሀገር ሰዎችም በቁጣ አይንህ አትመልከት።

፰. ወንድሟ ጳውሎስም በጸሎቷ የተናገረችውን ሰምቶ ፈጽሞ ደስ አለው በሥጋም ዘመዶቿ የሆኑት ቲቶ ፊልሞና ቀሌምንጦስም ደስ አላቸው።

፱. ከዚህም በኋላ ጳውሎስ ካህን ሆኖ ሌሎችም አገልጋዮች ሆነው በሀገራቸው ውስጥ ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ሰዎች ከንጉሡ ጋር አሳመኑ።

፲. በክህነት ሥራ ያገለገለ ጳውሎስም ተሠውረው የነበሩ አምስቱ አዕማደ ምሥጢራትን አስተማረ ንጉሡም አጽናኝ የሆነ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ በተቀበለ ጊዜ ራሱን ዘንበል አደረገ መለኮታዊ ምሥጢርንም አወቀ።

፲፩. ከዚህም በኋላ ኮርጅ አልብጅ ወደሚባሉ ሀገሮች ገባ ደግሞ በድንቁርና ጨለማ ውስጥ ወደሚኖሩ የከሐድያን ሀገር ገብቶ በወንጌል ትምህርት አበራላቸው ከዘመዶቻቸውም ከፈላስፎችና ከሌሎችም ብዙዎችን ወደ እምነት መልሶ የክርስትና ጥምቀትን አጠመቃቸው ይህም ወንድሟ ጳውሎስም እንደ ነጣቂ ተኩላ የነበሩትን ያማሩ የዋሃን በጎች አደረጋቸው።



Scanned with CamScanner

፲፪. ከዚህም በኋላ በክብር ባለቤት በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም በማርያም መግደላዊትም ስም አብያተ ክርስቲያናትን ሠሩ በዚያም ሀገር ታላቅ ደስታ ሆነ፡፡

፲፫. ማርያም መግደላዊትም ወንድሟ ጳውሎስን ለኋላ ዘመናት የሚሆን ወንጌል እንደሚያዝ ሕጉንና ሥርዓቱን ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን መመሪያ ሥራ አለችው፡፡

፲፬. እርሱም የሚያስፈልጉ መጻሕፍትን ወንጌልንም አዘጋጀ ዳግመኛም ለመሥዋዕት ሥራ የሚሆኑ ጻሕሎችን ጽዋዎችን ብዙ ሕብረ /መልክእ/ ቀለማት ያላቸውን ድባቦችን ሠርቶ አዘጋጀ፡፡

፲፭. ቁርባንን አዘጋጅቶ ክቡር ከሆነ ምሥጢር ከሥጋው ከደሙ አቀበላቸው፡፡

፲፮. በዚህ ሀገርም ቅዱሳት መጻሕፍትን እያስተማሩ ብዙ ወራቶች ተቀመጡ ጳውሎስም ቀሳውስትንና ዲያቆናትን ሾመ የተሾሙ እሊህንም ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግሉ አደረጋቸው፡፡

፲፯. እሊህ ሕዝቦችም ሃይማኖታቸው የጸና ምግባራቸው የቀና የሆነ የእግዚአብሔር አገልጋዮችም እንደሆኑ የታወቁ ሆኑ፡፡

፲፰. ከዚህም በኋላ የተሾሙትን ካህናት ጳውሎስና ማርያም መግደላዊት እንዲህ አሏቸው እኛ ወደ ሌላ ሀገር እንሄዳለንና የክብር ባለቤት በሆነ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖት ጽኑ የእግዚአብሔርም ሰላም አብሯችሁ /ይሁን/ ይኑር የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ በረከት የነቢያት የሐዋርያት የአባቶች የአብርሃም የይሥሐቅ የያዕቆብ በረከት የጻድቃን የሰማዕታት የሚካኤል የገብርኤልም በረከት አምላክን የወለደች የቅድስት ድንግል ማርያምም በረከት ለዘላለሙ በላያችሁ ይደር አሜን፡፡



Scanned with CamScanner

፲፱. ይህንም በሰሙ ጊዜ ከእነርሱ ስለመለየታቸው ሕዝቡ ሴቶችም ወንዶችም እያዘኑ በፍቅር በሰላም ሸኙአቸው እንዲህም አሉ እኛን አገልጋዮቻችሁንና ሕዝቡን በየዕለቱ በየሰዓቱ ሰላማችሁ ይጎብኘን ለዘላለሙ አሜን፡፡

# ምዕራፍ አምስት
# የመጋቢት ወር

አንድ አምላክ በሆነ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እናምናለን አሜን

፩. ከዚህ በኋላ እነ ጳውሎስ ሄደው ብዙ ከሐድያን ወደሚኖሩበት በራንጥያ ደሴት ገቡ፡፡ ማርያም መግደላዊትም እንደ ሐዋርያት በወንጌል ቃል ሰበከች ከሀድያንም በአዩ ጊዜ ይገርፏት ዘንድ ያዟት እንዲህም አሏት፡፡ አንቺ ከወዴት ነሽ? ከአጵሎንና ከአቴና በቀር ማንን ታመለኪያለሽ እነርሱም ጠላቶቻችንን የሚዋጉልን ናቸው አንቺም ለአማልክቶቻችን ስገጂ መስገድን እንቢ ካልሽ ግን ከእስር ቤት እንጨምርሻለን ከእጃችንም የሚያድንሽ የለም፡፡

፪. ማርያም መግደላዊትም እንዲህ አለቻቸው ከወርቅ ከብር የተሠሩ አማልክቶቻችሁ አፍ አላቸው አይናገሩም ዓይን አላቸው አያዩም ጆሮ አላቸው አይሰሙም አፍንጫ አላቸው አያሸቱም እጅ አላቸው አይዳሰሱም እግር አላቸው አይሄዱም በጉሮሮአቸውም ትንፋሽ የለም፡፡

፫. በሰማይ በልዕልና የሚኖር ፈጣሪዬ ጥላውን በፀሐይ ውስጥ ያኖረ እርሱም ይገድላል ያድናል ይቀስፋል ይቅርም ይላል፡፡ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም፡፡

፬. ዳግመኛም ስሙ ልንገራችሁ ሰማይና ምድርን ባሕሩንና ጥልቆችን የሚታየውንና የማይታየውን ማን ፈጠረ የሰማይን ርዝመት የሚያውቅ ማን ነው? የሰማይ



Scanned with CamScanner

ከዋክብትንና የባሕር አሸዋን ከብቻው ከእግዚአብሔር በቀር ቁጥራቸውን የሚያውቅ ማን ነው እርሱም እንደወደደ ይሠራል እንደአሰበውም ይፈጽማል እንዲህም አስተማረቻቸው። እነርሱም ይህን ትምህርቷን ሰምተው በርሷ ላይ ተቆጡ ወታደሮችም ይዘው የኂሊት አሠሯትና ጽኑ የሆነ ሥቃይን አሠቃዩአት።

፳. ከዚህም በኋላ ቁጥር ስፍር የሌላቸው ድንቆች ተአምራትን አደረገች። ከእነርሱ ጋርም የሚኖር አንድ በሽተኛ መጻጉዕ ነበረ እርሱም እንዲህ ሲል ለመናት እናት ሆይ አምን ዘንድ ለአምላክሽም እሰግድ ዘንድ ይህን በእኔ ላይ ያለ በሽታ አስወግጂልኝ እስዚህ አማልክት ግን እኔን ማዳን ተስኖአቸዋልና ጥቅም የላቸውም።

፳፩. የከበረች ማርያም መግደላዊትም ኢዮብን እንደፈወሰው በይቅርታው በምሕረቱ እግዚአብሔር ይፈውስህ አለችው እንዲህም በተናገረችው ጊዜ ከበሽታው ዳነ። ለእርሷም አገልጋይዋ በመሆን ሀገሩንና ሰፈሩን ትቶ በኋላዋ ተከተላት።

፳፪. ቤተሰቦቹም በሰሙ ጊዜ ይዘው ሰቀሉት። እንዲህም አሉት አንተ ሰው ከስቅለት ማን ያድንሃል ያቺ አቅም የሌላት ጦም አዳሪ ሥራየኛ ሴት ታድንሃለችን? ያም ሰው እንዲህ አላቸው እኔንም እርሷንም በፈጠረ በምታመልከው አምላኳ አምናለሁ ይህንንም በስሙ ጊዜ እንደተሰቀለ ብቻውን ትተውት ሄዱ።

፳፫. በሌሊት እኩሌታም አንበሶች መጡ ከተሰቀለበት አወረዱት። ንጋት በሆነም ጊዜ እንዚህ የሰቀሉት ሰዎች የሰቀሉትን ሰው ሊያዩት መጡ ከእርሱም ጋር አንበሶችን አገኙ ባዮአቸውም ጊዜ ፈርተው ወደ ኋላ አሉ ፍርሃትና መንቀጥቀጥ ይዟቸዋልና አንበሶችም ወደእነዚህ ሰዎች ሩጠው

ጭንጭናቸውን ያዙአቸው ሥጋቸውንም በሉ ደማቸውንም ላሱ አጥንቶቻቸውንም በምድር ሁሉ በተኑ።

፱. ከዚህም በኋላ እሊያ አንበሶች ማርያም መግደላዊት ወደአለችበት እስር ቤት ሄዱ ባርያ ለጌታው እንደሚሰግድም ሰገዱላት እርሷም እግዚአብሔር ይጠብቃችሁ ወደ ቦታችሁ ሂዱ አለቻቸው እነርሱም እየተቀዳደሙ ወደ መኖሪያቸው ሄዱ። እርሷ ግን ሰባት ቀኖት በእስር ቤት ኖረች ፊቷም እንደሚያበራ እንደንጋት ኮከብ ብሩህ ሆነ።

፲. ያም አንበሶች ከስቅለት ያወረዱት ሰው መጥቶ እጅ ነሣት እንዲህም አላት ዘመዶቼና ቤተሰቦቼ ሰቅለትን ሰቀሉኝ አንበሶችም መጥተው ከተሰቀልኩበት አወረዱኝ እነዚያንም የሰቀሉኝን ሰዎች በሉአቸው ደማቸውንም ላሱ አጥንቶቻቸውንም በተኑ ይህንም ያዩ የሰሙ ተደነቁ እንዲህም ቅድስት ማርያም መግደላዊትን ተነጋገሩት።

፲፩. ከዚህም በኋላ እሊያ ከሐድያን እንዲህ አሉ ይቺ ሥራየኛ ሴት ያደረገችውን ስሙ እንንገራችሁ በላያችን አንበሶችን በመስደድ አገራችንን አጠፋች ሰዎችንም አስጨረሰች። ሕዝቡም ሰምተው ከሀገራችን አስወጥተን ወደ ሌላ ሀገር እንሰደዳት አሉ ከሀገራቸውም አስወጥተው ሰደዱዋት።

፲፪. እርሷም ግን በሌላ ቦታ ሆና በአናብስት ተበልተው ስለሞቱ ሰዎች እንዲህ ስትል ጸለየች አቤቱ አልዓዛርን ከአራት ቀኖች በኋላ ከመቃብር ያሥነሣኸው ፈጥረህ የምትገዛ መሆንህና የይቅርታህ ገናንነት ይታወቅ ዘንድ እሊህ ባሮችህን አሥነሣቸው እነርሱም ተነሥተው በዚህም ዓለም በሚመጣውም ዓለም አገልጋዮች ባሮችህ ይሆኑ ዘንድ።

፲፫. ወንድሟ ጳውሎስም ወደርሷ መጣ እርሱም እንደስሙ ትርጓሜ አንደበቱ እንደሸቶ መዓዛ ጣፋጭ የክርስቶስም አንደበት የሆነ የሕይወትም ምንጭ የጥበብ አዘቅት



Scanned with CamScanner

የቤተክርስቲያንም መብራት ለበጎ ነገርም ታዛዥ የተባለ እርሱም እንዲህ አላት ተስፋ ያደረግሽው ሰማያዊ መንግሥትን አምላክሽን ከአገለገሉትና ደስ ካሰኙት ጋር ትቀበዩ ዘንድ አለሽና አይዞሽ አትፍሪ ልብሽም አይደንግጥ እኛም ልጆችሽ በጸሎትሽ ሰማያዊ መንግሥትን እናገኝ ዘንድ ተስፋ እናደርጋለን በረከትሽም ከእኛ ጋር ይኑር ለዘላለሙ አሜን።

## ምዕራፍ ስድስት

አንድ አምላክ በሆነ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በሚያዝያ ስድስት ቀን የሚነበብ የቅድስት ማርያም መግደላዊትን ገድል እንናገራለን።

፩. ይህንንም ሰምታ ፈገግ አለችና እንዲህ አለችው ወንድሚ እኔስ የገሃነምን ዜናዋን በምሰማ ጊዜ ልቤ ደነገጠብኝ የምድር ሥቃይ ኃላፊ ነው። እርስዋና ወንድሟ ጳውሎስ እንዲህ ተወያዩ የሀገር ሰዎች ግን ትምህርታቸውን ሰምቶ መቀበልን እንቢ አሉና እንዲህም ዘበቱባቸው እነዚህ ሰዎችም ለሞተ ሰው ይጸልያሉ የሞተ ሰው ማስነሣት የሚችል ማነው? የተባረከች ቅድስት ማርያም መግደላዊትም እንዲህ አለቻቸው ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና ፈጣሪ ሊያስነሳቸው ይችላል።

፪. እነሆ ጸሎቷና ልመናዋ በሰማይ ተሰምቶ እነዚያ ሙታን በጸሎቷ ተነሡ። እግዚአሔርም እንዲህ አላት እነዚህን የሀገር ሰዎች ለድካምሽ ዋጋ ሰጠሁሽ። እነዚያም የሀገር ሰዎች የተነሡትን ሙታን በአዩአቸው ጊዜ እጅግ አደነቁ በዘመዶቻቸው ሕይወት ፈጽሞ ደስ አላቸው የክብር ባለቤት በሆነ እግዚብሔር አመኑ ማርያም መግደላዊትንም አከበሩዋት።

፫. ከሙታን ተለይተው የተነሡትንም እንዲህ ሲሉ ጠየቋቸው ጳውሎስና ማርያም መግደላዊት የሚሏቸው ሰዎች እንደሚሉት በእውነት እሳት በሰማይ አለን? እነዚያም ድነው የተነሡት እንዲህ ሲሉ መለሱ ስሙ እንንገራችሁ በክብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ የከበረች ማርያም መግደላዊትን የተከተላትን ሰው በሰቀልነው ጊዜ አንበሶች መጥተው ጭንጭናችንን ሰበሩንና ሁላችንም ሞትን ጥርስ ማፋጨት ወደአለበት ወደ ጨለማው ዳርቻ ወሰዱን ለጨለማውም ተመሳሳይ የለውም የእሳቱም ፈሳሽ ወንዝ እንደክረምት ፈሳሽ ወንዝ የበዛ ነው በውስጡም በጋም ሆነ ክረምት ቀንም ሆነ ሌሊት የለም።

፬. ደግሞ አንበሶች እባቦች ጊንጦች አሉ ጥርሳቸውም እንደብረት ችንካር ነው። ሁልጊዜም ዕረፍት የላቸውም ያንን ጨለማም የሚቃወመው የለም ህብሩም አይታቀውም ይህን ይመስላል ሊባል አይቻልም። የከበረች ይቺም ሴት መልኳ እንደ ፀሐይ የሚያበራ ቅላቷም እንደ ሮማን የሆነ በእጆቿ ጠቀሰችንና ወደ ሕይወት መንገድ መርታን ወደዚህ ቦታ ደረስን።

፭. ዳግመኛም እንዲህ አሏቸው ማን ይመስላችኋል ሌላ ወይም ይቺ ሴት እነርሱም ያለእርሷ ምንም ሌላ አናውቅም ከእንግዲህም በእርሷ አምላክ የክብር ባለቤት በሆነ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን ይቺም መንፈስ ቅዱስ ያደረባት ሴት ጠቃሚ ሆነችን። ጎልማሳ ጳውሎስም ሳሕዩ ደምግባቱ ያማረ አቋሙም የተደላደለ ፊቱም እንደ ሮማን ቅላቱም እንደ ጽጌ ረዳ ጽሕሙም ዙሪያ የሆነ ነው። እርሱም አስቀድሞ በኦሪት ሕግ የነበረ አዋቂ አስተዋይ የሆነ ስለርሷ ስለኦሪት ቀናተኛ የነበረ ነው።

፮. በከበሩ ሐዋርያት እጅ ያመኑ ምዕመናን ደቀ መዛሙርቱም እጅግ የበዙ ናቸው። ይቺ የከበረች ማርያም መግደላዊትም

በእግዚአብሔር ኃይል ሰፍር ቁጥር የሌላቸው ድንቆች ተአምራትን አደረገች፣ በሀገሮች ሁሉ ዞራ አስተምራ ብዙዎች የሆኑ የሀገር ሰዎችን አሳምናለች። ከዚህም በኋላ በእግዚአብሔር ፈቃድ ዳኃና ወደ ሚባል ሌላ ሀገር ሄደች ዜናዋም በሁሉ ቦታ ተሰማ።

፯. በአንዲት ዕለትም ቅዱሳን ወደርሷ መጡ ከውስጣቸውም በገድሉ መልካም የሆነ አረጋዊ ሰው አለ። ቁጥር ስፍር የሌላቸው ብዙ ወንዶችና ሴቶች ደናግል እጆቻቸውን በላይዋ ላይ ሲያደርጉ በመላእክትም አምሳል አክሊልን በራሷ ላይ ያኖሩ ነበር። መላእክቱም ሁሉ በዙሪያዋ ከበው ይሁን ይሁን ይደረግ እያሉ ሲያመሰግኑ ራዕይን አየ ያም አረጋዊ ከሽልብታው በነቃ ጊዜ አሰበ። እንዲህም አለ ይህ በረከት በዚች የንጉሥ ልጅ ላይ ያድራል እርሷም ለሁሉ መሪ ትሆናለች መታሰቢያዋን ለሚያደርግ ስሟን ለሚጠራ በጸሎቷ ለሚታመን። የፈለገውን ሁሉ ትፈጽምለታለች።

፰. ያም አረጋዊ ደግሞ እንዲህ አላት ብዙ ተጋድሎ ትጋደዪ ዘንድ አለሽ መከራ በአገኘሽ ጊዜ ዕፁብ ዕፁብ ብለሽ አታድንቂ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን ተግሣጽ አታድንቅ ብሏልና እምነትሽንም ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ጣይ /አድርጊ/ እንዲህ ብሎ በመራት ጊዜ ከቀድሞው የበረታች ሆነች እርሱም ጸልዮ በሰላም ሸኛት።

፱. ከዚህም በኋላ ወደ ሀገረ ዳኅና ሄደች የጠንቋይንም ዘመዶች አገኘችና ሀገራችሁና መንደራችሁ ወዴት ነው አለቻቸው እነርሱም ሀገራችን ይህ ዳህና ነው አሏት ዳግመኛም እንዲህ አለቻቸው እነግራችኋለሁና የአንደበቴን ነገር ስሙ ነገሬንም አዳምጡ ዓለሙም ፍላጎቱም አምሮቱም ሁሉም ነገር ኃላፊ ነውና። የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ ስሙ በእኔ ቃል በዚህ ወንጌል መጽሐፍ ቃል እመኑ አምናችሁም ፈጽሞ የማይጠፋ መንግሥትን ታገኙ ዘንድ

የእግዚአብሔርም ወዳጆች አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብም ወደአሉበት ትወጣላችሁ።

፲. እርሷም ተጋድሎዋ ድንቅ የሆነ የምታውቅና የምታስተውል የእግዚአብሔርን መጻሐፍት ብሉያትና ሐዲሳትን ጠንቅቃ የተማረች ናት። እነርሱም እንዲህ አሏት አንቺ ይህን ሁሉ ነገር በምን አወቅሽ? አንቺ ብዙ ነገርን ታውቂያለሽና የምታጠምድ ሥራየኛ ትመስያለሽ አንቺም ነገርን በማጣመም ለወጥመድ የምትሰጪ ነሽ ሰውንም የምትገድይበት አድነሽም የምታስነሽበት ወጥመዶች አሉሽ ንጉሥ አዳልንም አስቢው። እርሱ ቢያይሽና ቢያገኝሽ ሰቅሎ ይገድልሻል ወደ ገደልም ይጥልሻል ከእጁ የሚያድንሽ የለም የምንነግርሽን ብትሰሚ በሰላም ሂጂ ወደምትሺውም ቦታ አምላክሽ ያድርስሽ።

፲፩. እርሷም እንዲህ አለቻቸው እናንተም ሂዱ ወደ በጎ አምልኮቱ ይመልሳችሁ። እኔም ፈጣሪ እግዚብሔር ወደመራኝ ቦታ እሄዳለሁ። እነርሱም ጉዞሽ መልካም ይሁንልሽ አሏት በዚያን ጊዜም ወደከተማቸው ሄደች የንጉሥ ሎሌዎችም አግኝተዋት ሰላምታ ሰጧት እርሷም የእግዚአብሔር ሰላም ከእናንተ ጋር ይኑር አለቻቸው።

፲፪. ዳግመኛም እንዲህ አሏት አገርሽ ወዴት ነው? የማን ልጅ ነሽ ፊትሽ እንደጨረቃ ያማረ የተወደደ ነው። እርሷም እንዲህ አለቻቸው እኔስ የድሆች ልጅ ነኝ እናንተ ግን በመልካም ነገር አመሳሰላችሁኝ ነገራችሁም ወደ ልቤ ገብቷል።

፲፫. በእግዚአብሔር የተጠራሁ ነኝ እምነቴም በስሙ ነው። እንዲሁም ደግሞ የእርሱ የብርሃን እናት በሆነች በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም በአማላጅነቷ የማምን ነኝ እናንተም እንደ እኔ እመኑ አምናችሁም የዘላለም ሕይወትን ታገኙ ዘንድ የከበረች የመንፈስ

ቅዱስን ጸጋ ታገኛላችሁ። ፈጽሞ በማይጠፋ ሰማያዊ መንግሥት እግዚአብሔርን ከአገለገሉትና ደስ ካሰኙት ጋር አንድ ትሆናላችሁ። የሚወደውን ሥራ ከሠራችሁ በሰማያዊ መንግሥት እንደ ሐዋርያት ባለሟሎቹ ወዳጆቹ ትሆናላችሁ። እንዲህ አስተማረቻቸው በሚገባ አስረድታ ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር መለሰቻቸው።

፲፬. እነርሱም እንዲህ አሏት ለእኛ ግን ከአንቺ ጋር አንድ መሆን ይሻለናል እስከ አሁን ይዘነው የነበረ እንደሬት መራራ የሆነ ነው ከመብላትና ከመጠጣት በቀር የምናውቀው የሌለ ይህንንም ብለው አምነው ተከተሏት እኒህም የሀገር ሰዎች አምነው ክርስቲያኖች እስከ ሆኑ እግዚአብሔር የሚወደውንም እስከሠሩ ቤተ መቅደስም እስከአነጹ ድረስ የሀገር ሰዎችን ያስተማረቻቸው ማርያም መግደላዊት ጥፋት የሌለበት የነገሯ የጣዕሙ መዓዛ እንደ እንኮይ የሆነ እንደከበረ እንቁ ሁሉመናዋ የተወደደ ምግባሯ ያማረ ሃይማኖቷ የጸና ትምህርቷ እንደማር እንደሶከር እንደጊደር ወተት ጥሞአቸዋልና።

፲፭. ይህቺንም እናት ሰውን የምትመራ የዓለም ብርሃን ያደረጋት የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራው ዕፁብ ነው። እኛም መሐሪ ይቅር ባይ ወደ ሆነ እግዚአብሔር ትማልድልን ዘንድ ከሚነድ እሳት ከክፋዎች አጋንንትም ከወጥድማቸው እንድን ዘንድ እንለምናለን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ለዘላለሙ አሜን።

## ምዕራፍ ሰባት

አንድ አምላክ በሆነ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በግንቦት ወር በስድስት የሚነበብ የቅድስት ማርያም



Scanned with CamScanner

መግደላዊት ገድል ይህ ነው። ጸሎቷ በረከቷ ከሁላችን ጋር ይሁን ለዘላለሙ አሜን።

፩. አባቶች ከኖሩበት ከዚህ ዓለም የመውጣቷን ነገር እንጽፋለን ቅዱሳን ንጹሐን ስሆኑ ደናግልና ሄሮድስ ለገደላቸው ሕፃናት ወደ ተሰጠች ፍጹም ደስታን ወደምታስገኝ ሀገርም እንደሄደችና እንደገባች ሄሮድስ መንግሥቱን የሚወርሰው ስለመሰለው በጌታ በመቅናት የገደላቸው ናቸው። እርሷም ከእነርሱ ጋር ትጫወታለች ደስ ብሎአትም ወተትን እንደጠገበ እንቦሳ ትዘላለች።

፪. ኑ እጅ እየነሣናት እየሰገድን እናመስግናት እርሷ በመንግሥተ ሰማያት ደስታ ታሰጠናለችና በእርሷ ፍቅር ከተራቡ ከተጠሙ ወገኖቿ ከሆኑ አገልጋዮቿ ጋርም ትደምረናለችና በጸሎቷም የበደልነውን በደላችንን ትደመስሳለችና የከበሩ እጆቿ ይዳሱን ክርኩሰትም ያንጹን እንደበታችን በመለኮት ጨው የጣፈጠ ይሆን ዘንድ። በእርሷም ጨውነት ደዌያችንን ታርቅልን።

፫. ቅድስቲቱም ጸሎቷ ይጋረድልን ይቀድሰንም የንጽሕቲቱ ንጽሕናም ያንጻን መዓዛዋም ከክፉ የኃጢአታችን ሽታ ለይቶ ያጣፍጠን መግቢያችንም እርሷ ወደምትገባበት ታድርግልን በበዓሏ ዕለትም ከእኛ ጋር ሆና መሪ ትሁነን ሀገራችንና መንደራችንን ከሐሰተኛ ጠላት ታድንልን ትጠብቅልንም እግራችንንም ከጨለማ ድጥ እንቅፋት ትታደግልን የሚጣሉን የጠላቶቻችን አጋንንት መርዛቸውን ታቀዝቅዝልን ለዘላለሙ አሜን።

## ምዕራፍ ስምንት

፩. የክብር ባለቤት የሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከተከተሉትና ወደ መንግሥተ ሰማያት አዳራሽ ከገቡ ከሰላሳ ስድስቱ ቅዱሳት ሴቶች የተባረከችና የተመረጠች እርሷ

ሰማያዊውን ሙሽራ እንቀበለው ዘንድ ኑ ውጡ አለቻቸው እሊህም በክብር ባለቤት በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖት ያጌጡና የተሸለሙ የከበሩ ሴቶች የአወጣጣቸው ምክንያት እንዲህ ነው።

፪. የክብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዕውራንን ዓይን በመግለጥ /ማብራት/ ሐንካሶችን በትክክል እንዲራመዱ በማድረግ ለምጻሞችን በማንጻት ሙታንን በማንሣት የረከሱ አጋንንትን ከሰዎች ላይ በማስወጣት የዲዳዎችን አፍ በመፍታት ዶንቆሮዎችን እንዲሰሙ በማድረግ ድንቅ ተአምርን በአይሁድ ፊት እያደረገ በኢየሩሳሌም በዕብራውያን መካከል በተገለጠ ጊዜ ከሁሉ ሰው ልዩ ሆኖ ስለሚያምር ሳሕዩ ስለትምህርቱ ጣዕምና ስለአንደበቱ ቅልጥፍና በአምስት ገበያ የሚመጠኑ ሰዎች ተከተሉት በመካከላቸው ያደረገውን ድንቅ የሆነ የእጁን ተአምራት የቃሉን ትምህርት አይተው የእግዚአብሔርን ገናንነቱን እያደነቁ ያመኑ አሉ።

፫. ያን ጊዜ በአምስት ገበያ ከሚመጠኑት ውስጥ ሰላሳ ስድስቱን ሴቶች መረጠ ይቿንም የከበረች ማርያም መግደላዊትን ልብሳቸውን በእግዚአብሔር በበጉ ደም አጥበው ካነጹ ከከበሩ ሴቶች ሁሉ መርጦ ከፍ ከፍ አደረጋት አከበራትም።

፬. እርሷም ስለፍቅሯ ከእርሳቸው ፈጽሞ ትበልጣለች እርሷም መድኃኒታችን በተነሣበት ዕለት እርሱ ሞትን ድል አድርጎ የተነሣው የፈጠራት ፈጣሪዋ እንደሆነ አውቃ ፈጽማ አመስግናዋለች።

፭. በእናታችን በማርያም መግደላዊት ጸሎት የእግዚአብሔር አብ ምህረት የእግዚአብሔር ወልድ ፍቅሩ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አጽናኝነቱ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ከሁላችን ጋር ይኑር አሜን።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

አንድ አምላክ በሆነ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በሰኔ ወር በስድስት የሚነበብ የቅድስት ማርያም መግደላዊት ክብርዋንና ገናንነቷን የሚናገር ገድል ይህ ነው። ይቺም እናት የከበረችና ከፍ ከፍ ያለች በወንጌል ውስጥ የተጻፈችና በሁሉም ዓለም የተሰበከች ከሰላሳ አምስቱ ቅዱሳት አንስትም በክብር የበለጠች በእነርሱ ዘንድም የከበረች ናትና ልናከብራት ከፍ ከፍም ልናደርጋት በዓሏንም ልናከብር መታሰቢያዋንም በየወሩ ልናደርግ ይገባናል። እርሷም የክብር ባለቤት የእግዚአብሔር ጽኑ ምስክር ሆናለችና።

፩. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አካል መዳሠሥ ለማን ተቻለው ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል እናቱ ማርያም በዮርዳኖስ ውሃ ካጠመቀው ከዮሐንስ መጥምቅ በቀር ያን ጊዜ በነጭ ርግብ አምሳል መንፈስ ቅዱስ ወርዶ አባቱ አብም የምወደው ልጄ ይህ ነው። የሚላችሁን የሚያስተምራችሁን ስሙት እያለ ነበር።

፪. በከበረ ወንጌል ስሟን ይጥሩ ብሎ እርሱ መርጧታል አክብሯታልና አሁንም የቤተ ክርስቲያን ልጆች አክብሯት ምክንያቱም ይህንን ዓለም ንቃ ትታ ጌታችንን ተከትላ አገልግላዋለችና ነሐሴ ስድስት ቀንም በዓሏን አክብሩ ይሄውም የአረፈችበትና ከዚህ ዓለም የወጣችበት ነው።

፫. ዳግመኛም እንደሐዋርያት በዓል በየወሩ በዓሏን አክብሩ ሥርዓቷ እንደ ሥርዓታቸው በዓላቶቿም እንደ አባቶቻችን ሐዋርያት በዓል ይሁን። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአማላጅነቷ የምታድን እርሷን በሥጋ በነፍስ መዳኛ ትሆነን ዘንድ ሰጥቶናልና እኛም ለክብር ባለቤት ክርስቶስ የሆነችውን ልናከብራት ከፍ ከፍም ልናደርጋት ይገባል። እርሱ መርጧታልና አክብሮ ከፍ ከፍ አድረጎ

ለሰው ልጆች ምህረትን የምትለምን የምታማልድ አድርጓታልና።

፱. አሁንም የንጉሥ ልጅ በሆነች በማርያም መግደላዊት በጸሎቷና በአማላጅነቷ ያድነን በይቅርታውም ጋሻነት ይጋርደን ለዘላለሙ አሜን የቤተ ክርስቲን ልጆች የሆናችሁ የተወደዳችሁ አባቶች እናቶች ወንድሞች እህቶች ሆይ እግዚአብሔር የድህነት ምክንያት ቡሩካን አርጋብ የተባሉ ወላጆቿ እርሷን የወለዱልን ይቺን ቡርክት እንዲህ ሲል የሰጠንን ዕወቁ አስተውሉ መታሰቢያሽን ያደረገ ስምሽን የጠራ ወደ ቤተክርስቲያንሽም ገብቶ የተማፀነውን ከታናሽነቱ እስከ ሽምግልናው የሠራውን በደሉን ኃጢአቱን አስተሠርይለታለሁ በየሰባት ሰባ ጊዜ እተውለታለሁ።

፲. የክብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለእናታችን ለብፅዕት ማርያም መግደላዊት ቃልኪዳን እንዲህ ሲል ሰጣት በጸሎትሽ የታመነውን ይከተሉኝ ዘንድ እኔ በመረጥኋቸው ደናግል ሁሉ በጸሎታቸው የሚታመነውን እነዚህም የዮሳ እናት ማርያም የያዕቆብ እናት ማርያም ናቸው በሌሎችም ስማቸው ጺስ፣ አላጺስ አጋጺስ በሚባሉ በጸሎታቸው የሚታመነውን እነርሱም በሚያለመልም በሃይማኖት ዘይት መብራታቸውን አብርተው ሙሽራው በመጣ ጊዜ የተቀበሉትና የተከተሉት መንግሥተ ሰማያት ለመግባት የተዘጋጁ።

፲፩. ከእርሳቸውም ጋር ዘይትን ያልያዙ እነዚያ ሰነፎች ደናግል ግን እንቅልፍን በማብዛት ሙሽራው በመጣ ጊዜ ለመቀበልና ወደ ሠርግ ቤት ማለት ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ያልተዘጋጁ በላያቸው ደጃፉ የተዘጋባቸው ናቸው። እነርሱም አቤቱ አቤቱ ክፈትልን አሉ መልአክ መጥቶ

እንዲህ አላቸው ከባልንጀሮቻችሁ ጋር መትጋት ተስኖአችኋልና ከዚህ ሂዱ።

፯. እናንተም በዚህ ዓለም ውስጥ የምትኖሩ ይህን አስቡ ባለቤት ሌባ የሚመጣበትን ጊዜ እንደማያውቅ ክሊሊት አኩሌታ ቢሆንም ወይም በሌላ ሰዓት ቢሆን አታውቁምና አምላካችሁን ተግታችሁ ነቅታችሁ በሃይማኖት ቆማችሁ ጠብቁት። በመጣም ጊዜ ሲተጋ ያገኘውን በአርባ ዘመናት የሠራውን ኃጢአቱን ያስተሰርይለታል።

፰. ለእኛ በጎ ሥራ ለሌለን መልካም ሥራ ለመሥራትም ሐንካሳና ልምሾ ለሆን ጌታችን ለመዳን ምክንያትን ሰጥቶናል። ሥራችንም አመንዝራነት ወደ ጎልማሳ ሚስት መሄድ ሌብነት፣ ሐሜተኛነት፣ ትዕቢተኛነት መታጀር ቀናተኛነት ቂመኛነት ሐሰተኛነት ታካችነት ሞት በዓያችን እያለ ይህን ሁሉ እንሠራለን ከሞት በኋላም የሚብስ በገሃነም ውስጥ መሠቃየት እያለ እርስ በእርስ በመለያየት እንገፋፋለን። በዚህም ብደለኞች ነን።

፱. በዓለም ውስጥ የምትኖሩ ወንድሞቼ ሆይ ከዝሙት ከስካር ተጠበቁ መማለጃ (ጉቦን) የወርቅ ወለድን አትውደዱ የሠረቃችሁትንም መባ አድርጋችሁ ወደ ቤተክርስቲያን አታስገቡ መጽሐፍ ነቂርና ሐንካሳ ብሎታልና ወደዚላለም ጥፋትም እንዳይገባ ወለድና መማለጃ የሚበላ ከሥጋውና ከደሙ አይቀበል። እግዚአብሔርም ከጠላት ወጥመድ ያድናችሁ ይልቁንም እኛን ሕዝበ ክርስቲያኑንም ይጠብቀን ለዘላለሙ አሜን።

## ምዕራፍ አሥር

አንድ አምላክ በሆነ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በሐምሌ ወር በስድስት የሚነበብ የብፅዕት እናታችን

የአምላክ አገልጋይ የሆነች የማርያም መግደላዊት ገድልዋ ይህ ነው በጸሎቷ የሚገኝ በረከቷ ከሁላችን ከሕዝበ ክርስቲያን ጋር ጸንቶ ይኑር አሜን።

፬. ወደ ቀደመው ነገር ተመልሰን ቅዱሳን መላእክት ሚካኤል ገብርኤል እንዴት እንደረዱት እንነግራችሁ። የምሥራቹን የሚናገር የከበረ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ገብርኤል ጾሙ በሚባል ሀገር ስለቤተ ክርስቲያኗ ሕንፃ በበዓሏ ለማርያም መግደላዊት ተገለጠላትና ድንቆች ተአምራትን አሳየ የዚያች ሀገር ኤጲስ ቆጶስ አርኬላዎስ ምስክር ሆነ ይህም የመላእክት አለቃ የከበረ ገብርኤል በሁለት ወገን ድንግል የሆነች ወደ ከበረች አምላክን ወደ ወለደች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከ ለዚህም ታላቅ ምሥጢር የታመነ ስለማብሠሩም ለአምላካችን ልደት ክብር ከመላእክት ሁሉ አብልጦ የከበረ ነው። መልአኩም ወደርሷ ገብቶ ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ አለ፤ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነውና ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ።

፭. እርሱም ደግሞ ወደ ሠለስቱ ደቂቅ የተላከና ከነደደ እሳት የዳናቸው በእረዳታው እግዚአብሔርን ደስ ወደ አሰኙት ሰዎች (ቅዱሳን) ሁሉ የተላከ ነው። አሁንም እርስበርሳችን እየተናቀርን ከባልንጀሮቻችን ጋር ተስማምተን ጥላቻንም አርቀን በቀናች ሃይማኖት በንጹሕ ልብም ሆነን በዚህ ክቡርና ገናና በሆነ መልአክ በበዓሉ ፀሎት በዚህ ዓለም እንሰብሰብ እርሱ ይቅር ባይ እግዚአብሔርም በምሕረት ዓይን ተመልክቶ ይቅር ይለን ይምረን ዘንድ።

፮. ያለሳቸው አማላጅነት እርዳታ ማንም ሊድን አይችልም ስለኃጢአታችን ስርየት ከሰይጣን ወጥመድ እግዚአብሔር ያድነን ዘንድ ስሙ ገብርኤል ወደ ሚባል ወደዚህ ወደከበረ

መልአክ ፣ ገናና ክቡር ወደሆነውም ባልንጀራው ወደ ሚካኤልም በሹመታቸው በማዕረጋቸው ከፍ ከፍ ወደአሉ ወደሌሎች የመላእክት አለቆችም ዳግመኛ እንማልዳለን።

፱. የገብርኤል የስሙ ትርጓሜ አምላክ ሰው ሆነ ሰውም አምላክ ሆነ ማለት ነው። ለእረኞችም እነሆ የዓለም መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ ብሩክ የሆነ ዛሬ በዳዊት ከተማ /አገር/ ተወልዶላችኋል ብሎ የተናገረ ይህ መልአክ ነው።

፲. ዳግመኛም የምሕረት እናት በተባለች በከበረች አምላክን በወለደች በእመቤታችን ድንግል ማርያም አማላጅነት በማርያም መግደላዊትም ልመናና ጸሎት ጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን በአገለገሉ በሌሎችም ደናግል ጸሎት ይማረን ይቅርም ይበለን ለእርሱም ለእግዚአብሔር በአንድነቱ በሦስትነቱ ምስጋና ይሁን ለዘላለሙ።

## አርኬ

ሰላም ለቤትከ በሀገረ ዳህና ዘቀደሳ። አርኬላዎስ ኤጲስ ቆጶሳ ወገብርኤል ሰባኪ ምጽአተ ክርስቶስ አንበሳ ለበዓለ ቤትከ ማርያም በዘይትሌዓል ሞገሳ በዓለማርያም አንበረ ወልደ አብ በርዕሳ።

## ምዕራፍ አሥራ አንድ

አንድ አምላክ በሆነ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በሐሌ ወር በስድስተኛው ቀን የሚከበር የበዓል እናታችን ቅድስት ማርያም መግደላዊትን ዜና ዕረፍቷን እንናገራለን።

፩. የክብር ባለቤት የሆነ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደተከተለችው እንነግራችሁ ዘንድ የክርስቲያን ወገኖች ስሙ። አስቀድሞ ግን እንደሌሎች ሁሉ በኃጢአ ከመሞከር ይልቅ የኢየሱስ ክርስቶስ ሙሽራ ትሆን ዘንድ መረጠች። እንደ ጳውሎስና እንደወንድሞቿ ሐዋርያት

የዚህን ዓለም ሐሳብ ንቃ ተወችው እነርሱም የዚህን ዓለም ክብር ንቀው አቃልለው በሰማያት የሚገኘውን ተድላ ደስታ መርጠዋልና፡፡

፪. ከወንድሟ ከጻውሎስም ጋር ምንም ቁጥር የሌለው ተጋድሎ ተጋደለች፡፡ የተጋድሎዋም ዜና ለማሰማው ዕፁብ ድንቅ ነው ነገር ግን የተቻለኝን ያህል ጥቂት እንነግራችኋለን ይቺም ማርያም መግደላዊት የክብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ቤቷን ገንዘቧን ትታ በተከተለችው ጊዜ ከርሷ ሰባት አጋንንት አውጥቶ እንደጣሉ አጠፋቸው እርሷም ኃጢአተኛውን ጻድቅ አመንዝራውን ድንግል የሚያደርገውን የፍጥረትን ሁሉ ጌታ የነገሥታት ንጉሥ የአማልክት አምላክ የሆነውን አገለገለችው፡፡

፫. ጌታችንም ከዐረገ በኋላ ፍለጋቸውን በመከተል ሐዋርያትን ታገለግል ነበር፡፡ ከዚህም አስቀድሞ በጌታችን በመከራው ጊዜ በስቅለቱና በሞቱ በሚቀብሩትም ጊዜ ነበረች አልተለየችም፡፡ በሰንበት ዕለትም ማለዳ ፈጥና ወደመቃብሩ ገሥገሥች ድንጋዩም ተንከባሎ የእግዚአብሔር መልአክ በላዩ ተቀምጦ አይታው ፈራች፡፡

፬. ጓደኛዋ የዮሳ እናት ማርያም ነበረች፡፡ መልአኩ እንዲህ አላቸው እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ክርስቶስን እንደምትሹት አውቃለሁ እነሆ ትንሣኤል ከዚህ የለም ለዚችም ለማርደያም መግደላዊት ዳግመኛ የክብር ባለቤት መድኃኒታችን ክርስቶስ ተገልጾላት እንዲህ አላት ወደ ወንድሞቼ ሂደሽ ወደ አባቴ ወደአባታችሁ ወደ አምላኬ ወደ አምላካችሁ አርጋለሁ አለ ብለሽ ንገሪያቸው አላት፡፡

፭. ወደ ሐዋርያትም ደርሳ የክብር ባለቤት የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የመነሣቱን ነገር አበሠረታቸው ንገሪ እንዳላትም ነገረቻቸው እርሷ ከእርሳቸው ቀድማ መድኃኒታችንን በማየቷ በእነርሱ ላይ አልተመካችም፡፡



Scanned with CamScanner

፯. ከዚህም በኋላ በሃምሳኛው ዕለት የእውነት መንፈስ አጽናኝ የሆነ ጰራቅሊጦስ በሐዋርያት ላይ በወረደ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ከወገኖቿ ጋር ተቀበለች ነቢዩ ኢዩኤል በትንቢቱ እንደተናገረ እንዲህ ሲል በሰው ሁሉ ላይ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስን አሳድርበታለሁ ልጆቻችሁ በልዩ ልዩ ቋንቋ ትንቢት ይናገራሉ።

፰. በወንዶችና በሴቶች አገልጋዮቼ ላይ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስን አሳድርባቸዋለሁ ከሐዋርያትም ጋር ዞራ በማስተማር ብዙዎች ሴቶችን መልሳ የክብር ባለቤት የሆነ ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖት አስገባቻቸው። ሴቶችንም ስለማስተማር ዲያቆናዊት ብለው ሾሟት ከአይሁድም ብዙ ተግዳሮት ግርፋት መንገላቱልም ጽኑ የሆነ መከራ በላዩዋ ደረሰ።

፱. ከዚህም በኋላ ተሰዳ ወደሮም ሄደች የጌታንም ሰው መሆን መከራ ተቀብሎ ተሰቅሎ መሞቱንና መነሣቱን ወደ ሰማይ ማረጉንም ሰበከች ብዙዎችንም አሳምና የጣዖቶቻቸውን ሕንፃና ምስል አፈረሰች የጥንቆላ ስፍራንም ባዶ ሰበረች እነርሱንም በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሳምና ለጥምቀትና ለንስሐ አበቃቻቸው።

፲. የበጎ ሥራ ጠላት ቀናባት ከአመንትም ተለይተው የቀሩት ወደ ከሐዲው ንጉሥ እንድርያኖስ ሄደው እንዲህ ሲሉ ነገር ሠሩባት ማርያም መግደላዊት የምትባል ክርስቲያን ሴት አለች እርሷም የጥንቆላ ስፍራን በሃይማኖቷ አሳመነቻቸው።

፲፩. ያ ከሐዲ ንጉሥም በሰማ ጊዜ ወደርሱ ያመጧት ዘንድ ከጭፍሮቹ ውስጥ ላከ ማርያም መግደላዊትም ወደ አለችበት ደርሰው ንጉሥ ይጠራሻል አሏት እርሷም እሺ ብላ ተነሣች ብዙ የሆኑ የትምህርቱ ሃይማኖት ልጆቿም

በኋላዋ ተከተሏት እርሷም የክብር ባለቤት የሆነ የክርስቶስን መከራ መስቀል ትቀበል ዘንድ ትቸኩል ነበር።

፲፩. ስትጓዝም እንዲህ እያለች ትዘምር ነበር ሙሴ ደርሼ የፈጣሪዬን ፊት አያለሁ በቀንና በሌሊትም እንባዬ ምግብ ሆነኝ እንዲህም እየዘመረች ወደዚያ ከሐዲ ንጉስ ሄደች ያ አላዊ ንጉሥም እንዲህ ሲል ጠየቃት ስምሽ ማነው? ሀገርሽስ ወዴት ነው? የአባትሽና የእናትሽ ስም ማነው? የአባትሽ ሀገርስ ወዴት ነው እንዲህ አላችው።

፲፪. የሚቀድመው ስሜ ክርስቲያን መባል ነው። አባትና እናቴ የሰየሙልኝ ግን ማርያም ብለው ነው ይህም ምን ታምር ማለት ነው የመንፈሳዊ አባቶቼ ስም ሐዋርያት ነው እነርሱም በክርስቶስ ስም ማመንን የለገሱኝ ናቸው። እኔ በመግዶል ሀገር ከደጋጎች ወገን የሆንኩ ነኝ የክብር ባለቤት የሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቸርነት ለእግዚአብሔር ንጹሕ መሥዋዕት እሆን ዘንድ ወደ ሀገራችሁ አደረሰኝ አለቻቸው።

፲፫. በክብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖት ልጇ የሆነች ጤቅላን ጠራቻት ከእርሷ ጋርም ያሉት ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሕዝቦችን ሴቶችንም ልጆችንም ከርሳቸው ውስጥ የታወቁና የተመረጡ ሦስት መቶ ሃምሳ ሶስት የሆኑትን እንዲህ አለቻቸው ወንድሞቼ እህቶቼ የሆርጉ ቀን ደርሷልና ልባችሁ አይሸበር ንጉሡ ከሚያመጣው ስቃይ እንዳይፈሩ ይህን ብላ አጸናቻቸው።

፲፬. ያ ንጉሥም ማርያም መግደላዊትን እንዲህ አላት እንዳላሰቃይሽ ጥልቀቱ ወደማይደረስበት ወደ ጥልቅ ገደል እንዳልወረውርሽና በጥርሳቸው ለሚናከሱ ለዘንዶዎች ለሚናደፉ ለእባቦች ለጊንጦች ሲሳይ እንዳትሆኚ ለእኔና ለአማልላክቶቼ ስገጂ። እርሷም እንዲህ አለችው። መልካም

ብስሃል ስእኔም ነገርህ ከማር ከሶከሬ ከወተትም ይጥማኛል እኔ ከአንተ ዘንድ ለአንገቱ ሰይፍን ተመኝቻለሁ።

፲፫. ዳግመኛም እንዲህ አለኝ ሰይፍን ፈለግሽን? እኔ ነበልባሉ ስለ ከንድ ከፍ ወደሚል እሳት እጨምርሻለሁ። እንጂ ሰይፍ የለም የሚያድንሽ ማነው? እርሷም በፈጣሪዬ ኃይል እኔ እሳቱን እንደቀዝቃዛ ውሃ አደርገዋለሁ ብላ ለንጉሡ መለሰችለት። ንጉሡም እንጨት ፈልጠው ያመጡ ዘንድ ሁለት መቶ ሰዎችን አዘዘ። እነርሱም አምጥተው አመጣን ብለው ነገሩት እሳት አንድዱ አላቸው። እንዳዘዛቸውም አነደዱና እንዳዘገዘን አደረግን አሉ።

፲፬. ንጉሡም በእሳቱ እንድትቃጠል ያቺን ሥራየኛ ሴት አምጧት አለ ወስደው አቀረቡአት ወዲያውኑ በፊቱ ቆመች እርሱም በእሳት እንዳትቃጠዪ ለእኔና ለአማልክቶቼ ስገጂ አላት ማርያም መግደላዊትም ከአንተ ዘንድ ሞትን እንደፈለግሁ አስቀድሜ ነግሬህ የለምን? አለችው ሂጂ ወደ እሳት ግቢ አላት እርሷም እሺ አለችው።

፲፭. ያን ጊዜም የአናንያ የአዛርያ የሚሳኤል አምላክ እነርሱን ከነደደ እሳት ያዳንካቸው እኔን ባርያህንም አድነኝ በፊትህና በባለሟሎችህ ፊት አታሳፍረኝ እያለች በፍጥነት ሄዳ ወደ እሳቱ ውስጥ ገብታ ቆመች እሳቱም እንደ ውሃ ቀዘቀዘ ፊቷም እንደ አጥቢያ ኮከብ እያበራ ከእሳቱ ውስጥ ወጣች። ከዚያም የነበሩ ሕዝቦች አጀንቱ እስሌቶችም የክብር ባለቤት በሆነ በጌታችን አምነው በኋላዋ የሚከተሏት ሆኑ።

፲፮. ንጉሡም በእነርሱ ላይ ተቆጣ እሊያን አምነው የተከተሏትንም እንዲያመጧቸው በአንገታቸውም የብረት ዛንጅር አስገብተው ያስሯቸው ዘንድ ጭፍሮቹን አዘዘ። ጭፍሮችም እንዳዘዛቸው አደረጉ ዳግመኛም አምጧቸው አለ። አምጥተውም በፊቱ አቆሟቸው እርሱም ወደ እኔ ተመለሱ ካልተመለሳችሁ ወደ ገደል እጨምራችኋለሁ



Scanned with CamScanner

አላቸው። እሲያ አገልጋዮችም እኛ ከእርሷ ጋር በግልጥ እንሞታለን እንጂ ወደ እንተ አንመለስም አሉት እርሱም እንገታቸውን አስሯቸው አለ ጭፍሮችም እንዳዘዛቸው አደረጉ።

፲፱. በማግስቱም ያ ንጉሥ ማርያም መግደላዊትን ጠርቶ እንዲህ አላት ልጄ ሆይ ነገሬን ስሚኝ ለመብላት እሩቅው የተከፈተ ለነገ የማያሳድሩ የተራቡ ኃይለኞች አናብስት አሉ በላይሽ ብሰዳቸው ሥጋሽን ይበላሉ አጥንቶችሽንም ይሰብራሉ በታትነውም ያጠፉሻል እርሷም የእውነተኞች አገልጋዮችህን ሥጋቸውን ለዱር አራዊት ምግብ አደረግ ብሎ ዳዊት በመዝሙሩ እንደተናገረ በርሳቸው ተበልቼ መሞትን እኔ እሻለሁ። ብላ መለሰችለት ያ ንጉሥም እንዴት እንደማሰቃየት እስከመከር ድረስ በእስር ቤት እስከ ሰባት ቀን አጽንታችሁ እስሯት አለ።

፳. እነዚያም የንጉሥ ጭፍሮች ማርያም መግደላዊትን እንዳትሞቺ ወደ ሀገሩ ንጉሥ ተመልሰሽ ስለ ንጉሥ ስበኪ በራቱም ስገጂ አሏት እርሷም ሕይወት አለኝ እንጂ ሞት የለብኝም አለች ወዲያውም ይዘው ወደ እስር ቤት አስገቧት። ሰንሰሉቶችን በማጥበቅና ከልብስ በማራቆት አስጨነቋት ልብሷም የአንበሳ ፀጉር ሆነላት ምግቧም የገዳማውያን አባቶች ምግብ ሆነላት።

፳፩. መላእክትም ሰማያዊ ሕብስትን ያመጡላት ነበር። ከሰባት ቀናት ፍጻሜ በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ ወደርሷ ወርዶ ቅዱሳን መላእክት ጻድቃን ሰማዕታት ነቢያት ሐዋርያት ነፍስሽን በክብር ይቀበላሉና አይዞሽ አትፍሪ አላት ይህንንም ብሎ ክንፎቹን አልብሷት እስከሰባት ቀናት ከእርሷ ጋር ተቀመጠ። ከዚህም በኋላ ለስም አጠራሩ ስግደት የሚገባው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደማርያም መግደላዊት ወረደ ከእርሱም ጋር ብርሃናውያን መላእክት

እሉ ከመለኮቱ ግርማ የተነሣ ደነገጡኝ እሱም አስቀድሞ ወዳጄ ሆይ አይዞሽ አትፍሪ ለአንቺ ቃልኪዳን ልሰጥሽ መጥቻለሁ ወይማያልፈው ዘላለማዊው ዓለም ወስጄ ከድካም አሳርፍሻለሁ አላት።

፳፫. እርሷም የክብር ባለቤት ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ቃልኪዳን ልትሰጠኝ ፈቃድህ ሆኗል፡ ከሁሉ በፊት ነፍሴን በምን ትወስዳታለህ አለችው። እርሱም የምትሺውን ለምኚ አላት እኔ በሰይፍ ተሰይፎ መሞትን እሻለሁ አለችው ጌታችንም እንደወደድሽ ይሁንልሽ አላት።

፳፬. ዳግመኛም እንዲህ አለችው ጌታዬ ሆይ እለምንሃለሁ መታሰቢያዬን የሚያደርገውን ስሜን የሚጠራውን ቤተ ክርስቲያኔን የሚያሳንጸውን እስከ ስንት ትውልድ ትምረዋለህ የክብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም መታሰቢያሽን ያደረገውን ቤተ ክርስቲያን በስምሽ ያሳነጸውን እስከ አሥራ አምስት ትውልድ እምረዋለሁ። ወደ ቤተ ክርስቲያንሽ ሄዶ የጸለየውን እስከ ሰባት ትውልድ እምረዋለሁ አላት ልጅ ባይኖረው በቃል ኪዳንሽ በማመን ልጅ እሰጠዋለሁ።

፳፭. የገድልሽንና የትእምርሽን መጽሐፍ የጻፈውን ያጻፈውን ያነበበውን የተረጎመውን ያሰማውን የተሳለመውን መታሰቢያሽን ከሚያደርጉ ጋር የተቆጠረ አደርገዋለሁ በኅሊሴ ወር በስድስተኛው ዕለት በዕረፍትሽ በዓል እጅ በመንሳት በማህሌት የሚያመሰግኑ ሁሉ አሥራት ይሁኑሽ አላት።

፳፮. ስንዴውን ወይኑን ወይም ዕጣኑን ዘይቱን ሌላም የመሳሰለውን መባ አድርጎ የሚሰጥ ከእንቺ ጋር በግልጥ ይግባ። በበዓልሽ ዕለት የለመነኝን በደሉን እተውለታለሁ ምንም እንደ ባሕር አሸዋ የበዛ ቢሆንም ኃጢአቱ ይሰረይለታል አመንዝራም ቢሆን ነፍስ ገዳይም ቢሆን በየሰባቱ ሰባ ጊዜ እተውለታለሁ። ለቤተ ክርስቲያንሽ ጌጥን

ሁ ሽልማትን የሚያደርገውን የሚሰጠውንም ዕድል ፈንታው መታሰቢያሽን ከሚያደርጉና በበዓልሽ ቀን በማህሌት ከሚያመሰግኑት ጋር ቁጥሩም ከእርሳቸው ጋር ይሁን አላት።

፳፮. ጌታችን ለማርያም መግደላዊት እንዲህ ብሎ ቃል ኪዳንን ሰጣት ይህንንም ሰምታ ደስ አላት፤ የክብር ባለቤት እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን አመሰገነች። ዳግመኛም ማርያም መግደላዊት እንዲህ ስትል ለመነችው ጌታዬና ፈጣሪዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በኔ ነገሮችን ለፍጥረት ሁሉ የምትሰጥ በስሜ በታነጸ ቤተ ክርስቲያኔ አዳራሽ ዘንድ የተቀበረ ከቤተሰቡ ጋር እድል ፈንታው መሥዋዕትን በፊትህ ካቀረቡ ደጋጎች ጋር ይሆን ዘንድ እለምንሃለሁ አለች ጌታም ይሁንልሽ አላት።

፳፯. ቃል ኪዳንም ከገባላት በኋላ ሰላምታ ሰጥቷት በታላቅ ክብር ወደ ሰማያት ዐረገ እርሷም ከጌታችን ዕርገት በኋላ በሃያ ስድስት ዓመት ነሐሴ ስድስት ቀን በሰላም ዐረፈች ሥጋዋንም ሐዋርያት ገንዘው ቀበሯት። ስለ ትውልድ ልዩ አገሯ ሊባት ያለቦታ ሂዳ አስገኘቻቸው አምላክ ያመሰገኑት ሙሴ ሁሉ ዮሐንስ ሆፍና ሆሴዕ አሕዛብ በምርጫቸው ሐዋርያም አመለኩ እንድርያስ፥ አስገደላት፥ የምስክርነት ሰባት ሳቢናትም ተቀዳጀች በጸሎቷ የማታገኝ በረከቷ ከእኛ ጋር ይኑር ለዘላለሙ አሜን።

## ምዕራፍ አሥራ ሁለት

አንድ አምላክ በሆነ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በመስከረም ወር በስድስት የሚነበብ የቅድስት ማርያም መግደላዊት ገድል ይህ ነው። ጸሎቷና በረከቷ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን።

፩. በመጀመሪያው ሰንበት ተነሥቶ ሰባት አጋንንት ላወጣላት ለማርያም መግደላዊት ታያት አጋንንት ያሳደረባት ምክንያት መልክ መልካም ተወዳጅ እህት ነበረቻት። ወዲህ መውሰድ ወዲህ መወደድ እያለች ትቀናባት ነበር በዚህ

ምክንያት፣ ትጋትንት አድረውባት ነበር መንፈስ ጥዕቢት፣ መንፈስ ጽርፈት (ስድብ)፣ መንፈስ ቅናት፣ መንፈስ ትውዝፍት (የምንዝር ጌኝ) መንፈስ ዝሙት፣ መንፈስ ዘሚዝ፣ መንፈስ ሐሰት፤ ይህን ክፉ መንፈስ ያወጣላት ጌታ በሞት ጊዜ።

፱. ገና ጨለማው ሳይለቅ ወደ መቃብሩ ገሥግሣ ደረሰች ድንጊያው ከመቃብሩ አፍ ተንከባሎ አገኘችው ከባለሟሎ ከዮሐንስና ከጴጥሮስ ዘንድ ፈጥና ሄደች እንዲህም አለቻቸው ጌታዬን ከመቃብር አውጥተው ወስደውታል የወሰዱበትን ግን አላውቅም አለቻቸው ጴጥሮስና ዮሐንስ ወጥተው ወደ መቃብሩ ሄዱ፤ ሁለቱ ፈጥነው በሚሄዱ ጊዜ ዮሐንስ ጴጥሮስን ቀድሞት ወደ መቃብር ደረሰ ዘልቆ በተመለከተ ጊዜ መጎናጸፊያውን አገኘ፤

፲. ነገር ግን አልገባም ስምዖን ጴጥሮስም ተከትሎት ደረሰ ወደ መቃብሩ ገባ መጎናጸፊያውን ብቻውን ወድቆ አገኘ ሻሹንም እንደተጠመጠመ ለብቻው ከዚህ በኋላ ቀድሞ ከመቃብሩ የደረሰው ዮሐንስም ገባ ተንሣኤውንም አይቶ አመነ፤ ከሙታን ተለይቶ እንዲነሣ መጻሕፍት ያለውን ገና አላወቁም ነበርና።

፲፩. ከዚህ በኋላ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ሄደው ከቤታቸው ገቡ፤ ማርያም መግደላዊት ግን ከመቃብር አጠገብ ሁና ታለቅስ ነበር እያለቀሰችም ወደ መቃብር በተመለከተች ጊዜ ሁለት መላእክት ብሩህ ብሩህ ልብስ ለብሰው አየች የጌታችን ሥጋ ካለበት ቦታ አንዱ በራስጌ አንዱ በግርጌ ተቀምጠው እኒያ መላእክትም አንቺ ሆይ ምን ያስለቅስሻል አሏት ማንን ትሻለሽ እርሷም ጌታዬን ከመቃብር ወስደውታል የወሰዱበትን ግን አላውቅም አለቻቸው ይህን ተናግራ ወደ ኋላ ተመለሰች፤ የሐዘንተኛ አይን [illegible] ነውና ቆሞ አየችው ጌታ እንደሆነ አላወቀችም።

፰. አንቺ ሆይ ምን ያሳለትሰሻል ማንንስ ትሻለሽ አላት እርሷም አትክልት ጠባቂ መስሏት ነበር። ጌታዬ አንተ ወስደኸው እንደሆነ ንገረኝ አለችው ወደ እኔ አምጥቼ ሹቱ ዕቀባው ዘንድ ጌታም ማርያም አላት ተመልሳም በእብራይስጥ ቋንቋ ረቡኒ አለችው መምህር ሆይ ማለት ነው።

፱. የተግሣጽ አነጋገር ወደ አባቴ አልወጣሁምና አትንኪኝ አላት ነገር ግን ወደወንድሞቼ ሂደሽ ወደ አባቴ ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬ ወደ አምላካችሁ ዐርጋለሁ ብለሽ ንገሪያቸው እንጂ አላት ማርያም መግደላዊትም ሄዳ ለደቀ መዛሙርቱ ነገረቻቸው ጌታችንን አየሁት ይህንም ነገረኝ ብላ ተናግ ብለሽ ንገሪ እንዳላት ተናግ ብላ ነገረቻቸው ሐዋርያት ግን አላመኗትም እርሷ ግን በፍቅሩ እየተቃጠለች በሀዘን ሁል ጊዜ የሞቱን ነገር ታስብ ነበር። የበዕዕት የቅድስት የሰማዕቱ ክርስቶስ ጸሎቷና በረከቷ በሁላችን ይደር አሜን።

## ምዕራፍ አሥራ ሶስት

አንድ አምላክ በሆነ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በጥቅምት ወር በስድስት የሚነበብ የቅድስት ማርያም መግደላዊት ዜና ገድሏን እንናገራለን ጸሎቷ በረከቷ ከሀገራችን ከኢትዮጵያ ጋር እንዲሁም ከሕዝቦቿ ጋር ይሁን ለዘላለሙ አሜን።

፩. ያክብር ባለቤት የሆነ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የልደቱን ዜና በሁለት ወገን ድንግል የሆነች የእመቤታችን ማርያምን በገሊላ አውራጃ ካለች ከናዝሬት ወንጀለኛ ሄሮድስን ከመፍራት የተነሣ የመሰደዷን ነገር በሰማች ጊዜ በእርሷና በመድኃኒዓለም ልጁ በኋላቸው ትከተል ዘንድ አሰበች። በበረሃዎችም ውስጥ ስትገባ በመንገድ ሽምቀው የሚጠብቁ ሽፍቶች አዩዋት ይዘውም በሥጋ ግብር ሊገናኟት ወደዱ።

፪. እርሷም አይታ ደነገጠች ወደ ሰማይም ቀና ብላ እንዲህ ስትል ጸለየች የአናንያ የአዛርያ የሚሳኤል አምላክ መልአክህን ልከህ ከሚነድ እሳት ያዳንካቸው እንደርሳቸውም ከዚህ ጥፋት አድነኝ ሣራን ከጌራራ ንጉሥ ሶስናን ከረበናት

እጅ ሙሴን ከፈርዖን እጅ ዮሴፍን ከወንድሞቹ እጅ ያዳንክ እኔን መጻተኛ የሆንኩ ባርያህን አድነኝ ይህንንም ብላ በምድር ላይ በግንባሯ ፍግም ብላ ወደቀች፡፡ በዚያን ጊዜ አንበሳ ወደ ርሷ መጣ ባየችውም ጊዜ ይበላት ዘንድ ወደርሱ ሮጠች ወደ ገሃነም ከመውረድ በአውሬ ተበልቶ መሞት ይሻላል ብላለችና፡፡ እግዚአብሔርም የልቧን ጥንካሬ ባየ ጊዜ የዚያን አንበሳ ልብ አራራላት አንበሳውም ሲያት ሰገደላትና እንዲህ ሲል በሰው አንደበት ተናገረት፡፡

፫. በሕይወት ዘመኔ ሁሉ ላገለግልሽ ወደአንቺ መጥቻለሁና ቅድስት ሆይ አትፍሪ አላት እርሷም ሐዘኔ ወደ ደስታ ተመልሷልና እሺ በጎ አለችው ይህንንም እየተነጋገሩ መንገዳቸውን ተጓዙ እነዚያም የመንገድ ሽማቂዎች የፈለጉትን አላገኙም ባዩትም ነገር ፈርተው ተመለሱ፡፡

፬. ይቺም ማርያም መግደላዊት በዚያ አንበሳ ላይ ተቀመጠች እርሱ እንዲያገለግላት ታዟልና ያም አንበሳ ንግሥት ሆይ ወዴት ነው የምትሄጂው ፍላጎትሽ ምንድነው አላት እርሷም ፍላጎቴንስ እነግርሃለሁ የሰማይና የምድር ንግሥት የሆነች እመቤቴ ድንግል ማርያምን የዓለም ሁሉ ንጉሥ የሆነ ልጇንም እፈልጋቸዋለሁ ነፍሴንና ሥጋዬን በእጆቻቸው ውስጥ ጥያለሁና አለችው፡፡ በስደታቸው ልተባበራቸው እወዳለሁ፡፡

፭. ደግሞ እንዲህ አላት የቀድሞ ኑሮሽ ምን ነበር? እሷም የቀድሞ ኑሮዬ ከንቱ ነበር አለችው በአንዲት ሌሊትም የሚያስደነግጥ ክፉ የሆነ ራዕይን አየሁ ስለዚህም ነፍሴንና ሥጋዬን ሰማይና ምድርን በፈጠረ አምላክ እጅ በመጣል

የኃላፊውን ዓለም ኑሮ ትቼ የዓለሙን ሁሉ ንጉሥ አከተለው ዘንድ ወደድሁ አለችው፡፡

፮. ያ አንበሳም እንዲህ አላት አዎን እውነት ነው የክብር ባለቤት የሆነ የድንግል ማርያም ልጅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በኋላው የተከተለውን አመንዝራውን ድንግል ያደርገዋል ኃጥኡን ጻድቅ ያደርገዋል እንዲህም እየተናገራት ከፈለገችው ቦታ ጌታና እናቱ ካሉበት አደረሳት አንበሳውም ወደ መኖሪያው ዱር በሰላም ተመለሰ፡፡

፯. ይቺም የተመረጠችና በዘመድ የከበረች ሴት በምድር በተቦረቦረ ፍርኩታና በዋሻ ውስጥ የምትኖር ሆና ሥጋዋም እንደ እንጨት ቅርፊት የደረቀ እስኪሆን ድረስ በቁርና በውርጭ ሌሊትና ቀን ተግቶ በመጸለይና በመስገድ ሥጋዋን ስታደክም ኖረች ከብዙ ድካምና ላብ የተነሣም መልኳ የጠቆረና እጅግም የጠወለገና የከሳ ሆነ በዚህም ትደሰት ነበር፡፡

፰. አንዳንድ ጊዜም ቅጠል ትለብስና በተራራዎችና በጫካዎች ውስጥ ትዘዋወር ነበር፡፡ ከዚህም አስቀድሞ በዓለም ውስጥ ሳለች ደግ አዛኝ ነበረች ድሆች ምስኪኖች ወደሚኖሩበት እየሄደች ገንዘቧን ትመጸውታለች የተራቡ ያገኘች እንደሆነ ታበላቸዋለች የተጠማውንም ታጠጣዋለች እንግዳና መጻተኛውንም ተቀብላ ካላት ትመግባለች፡፡

፱. እንደዚህም ቀንና ሌሊት እየለመነች በጾጥታ ኖረች ልመናዋም ይህን ዓለም ንቀው ከተዉ ገንዘባቸውንም ለምጽዋት ሰጥተው ሙሽራውን ከተከተሉት ከአምስቱ ብልሆች ደናግል ጋር አንድ አንድትሆን መለመን ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ልመናዋን ሰምቶ እንዲህ አላት ድንግል የሆንሽ ወዳጄ የእኔንም ፍለጋ ትከተይ ዘንድ የተገባሽ ሆነሻል ደግሞ የእናቴ የማርያምን ፍለጋዋን የመላእክትም ፍለጋቸውን እነሆ እኔን ሄሮድስ ይፈለገኛል፡፡

፲. ያንቺም ዕድል ፈንታሽ ከእነዚህ ብልሆች ደናግል ጋር ይሁንልሽ ይህን ብሎ ከርሷ ተሠወረ። ሄሮድስም ሰምቶ እንዲህ ሲል ወደርሷ ላከ ያቺም ማርያም መግደላዊት ወደ ቤተልሔም ደርሳለች ሔዳለች ወደ እኔ አምጧት ብሎ ወደርሷ ላከ መልዕክተኞችም ሁሉም ያውቋት ነበርና ባዩዋት ጊዜ ደንግጠው ወደ እኛ የመጣሽ በደህና ነውን? ሄሮድስ ሁልጊዜ ይፈልግሽ ነበርና አሉዋት በሰማችም ጊዜ ደንግጣ እንዴት ይፈልገኛል? አለቻቸው።

፲፩. እነርሱም ለክፉ ነገር እንጂ ለበጎ አይደለም አንቺም ለብቻሽ የምትሞቺ አይደለምና ከአንቺ ጋር ስለተነጋገርን እኛንም ይገድለናል አሏት። በዚያም በቤተልሔም ዋሻ እህል ሳትበላ ውሃም ሳትጠጣ በዚያ አደረች በጸሎቷ የሚገኝ በረከቷ ሀገራችን ኢትዮጵያን ከጥፋት ይጋርዳት ለዘላለሙ አሜን።

# ምዕራፍ አሥራአራት

አንድ አምላክ በሆነ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በህዳር ወር የሚነበብ የቅድስት ማርያም መግደላዊት ገድል ይህ ነው። ጸሎቷና በረከቷ ከሁላችን ጋር ለዘላለም ይኑር አሜን።

፩. ከሌሊቱ እኩሌታም ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ተገልጾ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ በጠዋት ተነሥተህ ሕፃኑን ከእናቱ ጋር ይዘህ ወደ ግብጽ አገር ሽሽ ትላንት ወደዚህች ሀገር በደረሳችሁ ጊዜ ርኩስ መንፈስ ያደረበት አንድ ሰው አይቷችሁ እርሱ በፈረስ ጋልቦ ሄዶ ለሄሮድስ ነግሮታልና ጭፍሮች ወደዚህ ፈጥነው ይላካሉ ይደርሳሉና ዮሴፍ ሆይ እወቅ ተጠንቀቅ አለው።

፪. ወዲያው ተነሥቶ መልአኩ እንደ ተናገረው ለእመቤታችን ለድንግል ማርያም ነገራት በዚያን ጊዜም እመቤታችን ድንግል ማርያም ፈጥና ተነሣች ሕፃኑንም በጀርባዋ

አዘለችና አባቴ ዮሴፍ ሆይ ፈጠን ብለህ ተነሣና እንሂድ አለችው ያን ጊዜም ከሀገር ሰው ማንም ያያቸው ሳይኖር ሄዱ። ዘጠኝ ሰዓትም በሆነ ጊዜ ያችን ሀገር ሄሮድስ ከበባት የሀገሩን ሰዎችም ማርያም ወዴት አለች ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም አላየናትም ከሀገራችን ከሄደች ሶስት ወር ሆኗታል አሉት።

፫. ሄሮድስም እመቤታችን ድንግል ማርያምን ሕፃኑን መድኃኒታችን ክርስቶስን በቦታው ሁሉ በምድር ጉድጓድና በዋሻዎች በጨፈቁ ዛፎችና በዱር ውስጥ ይፈልጓቸው ዘንድ ወታደሮቹን አዘዘ። እርሳቸውም በዚህ ሁሉ ፈልገው አላገኙአቸውም ወደ ሄሮድስም ተመልሰው እንዳላገኟቸው ነገሩት ሄሮድስም የነገረውን ጠርቶ ማርያምን በየት ቦታ አየሃት አለው። እርሱም ትላንት በዘጠኝ ሰዓት በናዝሬት ውስጥ አይቻት ወደ አንተ መጣሁ። ማርያም መግደላዊትም ከርሷ ጋር አለች አለው። ንጉሡም ጭፍሮቹን ለምን ትዘብቱብኛላችሁ አላቸው። ይህንም ብሎ አንገታቸውን ይቆርጥ ዘንድ ድርናኤል የተባለ ሰያፊውን አዘዘው ወዲያው ቆረጣቸው የጨለማ መላእክትም መጥተው። ነፍሶቻቸውን ወደ ጨለማ ወሰዱ የሥጋቸውንም በድን ሙሴንና አሮንን እንደተጣሏቸው እንደዳታንና አቤሮን ምድር አፏን ከፍታ ሁሉንም ዋጠቻቸው።

፬. ሄሮድስም ያሉትን ሰዎቹን እንዲህ አላቸው የዚህ ሰው አማልክት በእኔ ላይ ተቆጥተዋል ይህንንም ተናግሮ የሀገር ሰዎችን ወንዶችንም ሴቶችንም ሁሉንም ያመጡአቸው ዘንድ ባሮቹን ጭፍሮቹን አዘዘ ባመጧቸውም ጊዜ አንገቶቻቸውን በሰይፍ እንዲቆርጡ አዘዘና ቆረጧቸው የተቆረጡትም ቁጥራቸው ዘጠኝ መቶ ሺህ ሆነ በመንግሥተ ሰማያትም የምስክርነት አክሊልን ተቀዳጁ



Scanned with CamScanner

ከዚያችም ሀገር ከሰው እስከ እንስሳ አንድም አልቀረ ከእንስሳትም የተቆረጡት ስድስት መቶ ሺህ ዘጠና ሰባት በሰይፍ የተገደሉትም ሁሉ ከሰማዕታት ጋር የተቆጠሩ ሆኑ። የሄሮድስም ጭፍሮች መላእክት ከሰማይ ሲወርዱና በተገዱለት ሰዎች በራሳቸው ላይ አክሊሎችን ሲያቀዳጇቸው አይተው እንዲህ ሲሉ ጮኹ ከእመቤታችን ከከበረች ድንግል ማርያም በተወለደውና ክርስቶስ ተብሎ በተጠራው /በሚጠራው/ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ አምላክ እናምናለን ሄሮድስ ሆይ እግዚአብሔር ለአገልጋዮቹ የሚሰጠውን ክብር አታይምን?

፳. ሄሮድስም እጅግ ተቆጣ አንገቶቻቸውንም በሰይፍ ይቆርጡ ዘንድ ጭፍሮቹን አዘዘና ቆረጧቸው የማይጠፉ የምስክርነት አክሊልን ተቀዳጁ ዳግመኛም የሰማዕታትን በድኖቻቸውን ይሰበስቡ ዘንድ ዕንጨቶችንም አምጥተው እሳትን አንድደው ወደ እሳቱ ይጨምሯቸው ዘንድ አዘዘ ጭፍሮቹም እንደአዘዛቸው እሳትን አንድደው አቃጠሉአቸው በዚያን ጊዜም የመላእክት አለቆች ሚካኤልና ገብርኤል ከሠራዊቶቻቸው ጋር ወርደው በእሳት ሰይፍ ቀሠፏቸው ቁጥራቸውም ስሳ ሰባት ነፍስ ሆነ እነዚህም በነፍስ በሥጋ የተጎዱ ናቸው።

፳፩. ከዚያም መላእክት የሰማዕታትን በድኖቻቸውን ወሰዱ የክብር ባለቤት በሆነ በጌታ ክርስቶስ ፊት አቆሟቸው ስለእርሱ የሞቱ እነዚያ እንስሳትንም የከበረች ድንግል ማርያም ወደአለችበት ወደ ሊባኖስ ሀገር ወስደው አኖሯቸው የመላእክት አለቃ ራጉኤልም እየጠበቃቸው እስከ ዛሬ አሉ። ከዚህም በኋላ ሄሮድስ ወደ ይሁዳ ሀገር ደረሰ። እንዲህ የሚል አዋጅ ነጋሪም ይዞር ዘንድ አዘዘ። ወንድ ሕፃን የወለደ ሁሉ ወደ እኔ ያምጣ የማያመጣ ቢኖር ጽኑዕ ሥቃይን ተሰቃይቶ በክፉ አሟሟት ይሞታል።



Scanned with CamScanner

፳. ስለዚህም ከግብጽ አውራጃ ወሰን እስከ ዮርዳኖስ ባሕር እስከ ዛብሎንና እስከ ንፍታሌም ሀገር ድረስ አዋጁን ሰምተው ፈርተዋልና ስለዚህ ሕፃናትን ሰብስበው አመጡ ሄሮድስም ገደላቸው የተገደሉትም ቁጥራቸው ሶስት ሚሊዮን አራት መቶ ዘጠና ሺህ ነው። በእናቶቻቸው ጡት ወተት ምድር እስክትነጣ ድረስ በሕፃናቱም ደም ወንዞች እስኪሞሉ እንዲህ ተገደሉ። የሰማይ መላእክትም ደንግጠው እሊህ ሕፃናት ምን አጠፉ ምንስ ክፉ ሥራ ሠሩ አሉ። ከልዑል ሕግዚአብሔርም ዙፋን ውስጥ እንዲህ የሚል ቃል ወጣ ኢየሩሳሌም በሰው ደም ትታጠብ ዘንድ እንዳላት እንዲሁ በነቢይ ተጽፎአልና እነዚህ ሕፃናት ግን ለመንግሥተ ሰማያት የተዘጋጁ ሆነዋል።

፳፩. ከዚህም በኋላ ሄሮድስ ሕፃናትን እንደገደለ ኤልሳቤጥ ሰማችና ደነገጠች ዘካርያስም ሰምቶ እንዲህ አላት ልጃችን ዮሐንስን ይዘሽ ወደሌላ ሀገር ሂጂ እኔ እያለሁ እርሱ ሊሞት አይገባምና እኔም የእግዚአብሔርን መንገድ ትቼ ሞትን መሞት አይባኝምና አንቺ ግን ልጅሽን ይዘሽ ወደወደድሽው ቦታ ሂጂ እግዚአብሔር ይረዳሻልና እህቴ አልሳቤጥ ሆይ እውነቱን ልንገርሽ በመንግሥተ ሰማይ በቀር በዚህ ዓለም አንተያይም ኤልሳቤጥም እያዘነች መንገዷን ሄች። ወደ በረሀ ደረሰች በአንዲት ድንጋይ ውስጥም ተቀመጠች።

፳፪. አንድ መርፌ ሻጭም በዚያ ነበር ወደ ንጉሥ ከተማ ሄዶ እንዲህ ሲል ነገር ሠራበት ዘካርያስ ልጁንና ሚስቱን ወደሩቅ አገር ላካቸው እርሱ ትዕዛዝህን አቃሏልና ለመንግሥትህም አይታዘዝም እርሱ ግን በምኩራብ ውስጥ ይኖራል ኑሮውም ሰላም ነው። ሄሮድስም አገልጋዮቹን ባሮቹን እንዲህ ብሎ አዘዛቸው ኑ ሂዳችሁ ያን ሰው ጠይቁት እውነት ከሆነም ግደሉት።

፲. እነዚህም ትእዛዙን ተቀብለው ሄዱ ከዚያም ምኩራብ አገኙትና በእርጅናህ የወለድኸው ልጅህ ወዴት አለ? ሚትህስ ወዴት ናት ብለው ጠየቁት ዘካርያስም በማስተዋል ፈገግ ብሎ እንደ እኔ ያለሸማግሌ አላያችሁምን? የነቢይ ሳሙኤል እናት በእርጅና ወለደች እንዴት በእኔ ላይ በመዘበት ትሳደባላችሁ አላቸው፡፡

፲፩. ያም ለሄሮድስ የነገረው አመጸኛ ዋሾ ምስክርን ትሻላችሁን? ይህ የሚናገረው ቃል ስለማርያም አይደለምን? አላቸው ዘካርያስም በሰማይም በምድርም ዕድል ፈንታዬ ከእመቤቴ ማርያም ጋርና ከተወዳጅ ጌታዬ ልጇ ጋር ይሁን አለ፡፡ የዚያን ጊዜም ይዘው በቤተ መቅደስ ውስጥ ገደሉት ደሙም እንደ ውሃ ፈሰሰ፡፡ በድኑንም በዚያ ጥለው ወደሄሮድስ ተመለሱ የሆነውንም ሁሉ ነገሩት፡፡

፲፪. ሄሮድስም መርፌ ሻጩን ሚስቱንና ልጁን ለምን አላመጣሃቸውም አለው እርሱም እንዲህ ብሎ መለሰ ከሄዱ በኋላ ሰማሁ እንጂ ሲሄዱ አላየሁም ፈልጌም አጣኋቸው ከዚያ በኋላም ወደ አንተ መጥቼ ነገርሁህ ሄሮድስም እንዲህ አለው ልጁንና ሚስቱን ካጣሃቸው ለምን አትተወውም ነበረ ንጹሕ ደምን ለምን አስፈሰስክ ይህንንም ተናግሮ ንጉሡ ራሱ በሰይፍ መታው፡፡ ነፍሱንም መላእክተ ጽልመት ተቀብለው ወሰዷት፡፡

፲፫. ዘካርያስም በነጭ ፈረስ ላይ ተቀምጦ በእጁም ቦግ ቦግ የሚል የእሳት ሰይፍ ይዞ ነፍሳት በሚሄዱበት መንገድ ያን ነገረ ሰሪ ሰው ተገናኘው የመላእክት አለቆች ሚካኤልና ገብረኤልንም በእኔና በዚህ ሰው መካከል ፍረዱ አላቸው፡፡ እነርሱም በሰይፍ የገደለ በሰይፍ ይሙት ተብሏል በያዝከው ሰይፍ እንድትገድለው ፈርደናል አሉ፡፡

፲፬. እርሱ ዘካርያስም መልካም ፈረዳችሁ ብሎ ያንን ሰው ከንጉሥ ጋር የምትኖር መስሎህ ነበር? ብሎ በእሳት



Scanned with CamScanner

ሰይፍ ገረፈውና ወደ ሶስት ቦታ ከፈለው ወደ ቀደመው ሁኔታውም ተመለሰ አሥራ አንድ ጊዜም ከፈለው መላእክትም ሚካኤልና ገብርኤል ዘካርያስን ጌታ እንደሠራው እስኪፈርድበት ተወው ወደ ሲኦል ይሂድ በዚያም ይኑር እርሱ የኃጢአተኞችና የአመጸኞች እድል ፈንታቸው ነው።

፲፭. ዘካርያስም ከመላእክት ጋር ወደ ሰማያት አረገ ደጋግ ሰዎችም መጡ ሥጋውንም በግምጃ ልብስ ገንዘው በቤተ መቅደስ ውስጥ ቀበሩት። የከበረች እመቤታችን ድንግል ማርያምም ዘካርያስን እንደገደሉት በሰማች ጊዜ ወደ ሰማይ ቀና ብላ በእርሱ ላይ ያደረግነው ክፋት ስለሌለ በእኛና በሄድሮስ መካከል አቤቱ ፍረድ ብላ ወደ ሊባኖስ ተራሮች ሸሸች ጸሎቷና በረከቷ ይድርብን አሜን።

## ምዕራፍ አሥራ አምስት

አንድ አምላክ በሆነ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን በታህሣሥ ወር በስድስት የሚነበብ የቅድስት ማርያም መግደላዊት ዜና ገድሏን እንናገራለን።

፩. ያቺ ማርያም መግደላዊትም ወደ ሌላ ጎዳና ፈቀቅ አለች ገዳማቱን በረሃዎችን በዓለም ያሉ ሀገሮችን እየዞረች ከጌታችን የክብር ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር ደርሳ ሰገደች እንዲህ ስትልም አመሰገነችው የአማልክት አምላክ የፍጥረቱ ሁሉ ጌታ ለአንተ ምስጋና ይገባል በላይና በታች በምልዓት በየብስና በባሕር የሚኖሩትን ሁሉ አንተ ቁጥራቸውን ታውቃለህ ለአንተም ምስጋና ይገባል እኔም መቄዶንያ ወደምትባል አገር እሄድ ዘንድ ወደድሁ ጣዖትን የሚያመልኩና የሚያሚርቱ ወንጀለኞች የሆኑ ብዙ ከሐድያን በዚያ ይኖራሉና እነርሱም በዱር በምሰሶ ወገብ በዘንዶ በእባብ እያሰሩ ከዋክብትን የሚያመልኩና

ወንጀለኞች የሚያሟርቱ ጠንቋዮች ናቸው ርስትና ዕድል ፈንታን ከዘካርያስ ጋር ዕድል ባገኝ እፈቅዳለሁና።

፪. ጠላታችን ሄሮድስ የክርስቲያኖችም ሁሉ ጠላት ጣዖትን የሚያመልክ ነው ሕዝቡም እንደርሱ የሚያመልኩ ናቸው። መልአክም ወደፈለግሽው በሰላም ሂጂ የእግዚአብሔር ቸርነት ከአንቺ ጋር ይኑር አላት ይህንንም ሰምታ ወደ መቄዶንያ ሄደች የሀገር ሰዎችንም ጣዖትን ሲያመልኩ አገኘቻቸው ጳውሎስ ወደዚች አገር በደረሰ ጊዜ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን እንዲህ እያለች ስትሰብክ አገኛት ስለመንግሥተ ሰማያት ራሳቸውን ድኃ የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው።

፫. ሚስት የሌላቸው ብፁዓን ናቸው እነርሱ እንደመላእክት ሆነው መንግሥተ ሰማያትን ይወርሷታል። የዘላለም ሐይወትን ያገኛሉ። እንዲህ ከጳውሎስ ጋር እየሰበከች ኖረች ይህንንም ትምህርት ሰምታ ስሟ ጤቅላ የምትባል በላቴና አመነች ያለመብልና መጠጥ ከቤቷ ደርብ ሳትወርድ ሶስት ቀኖች ኖረች። እናቷም እንዲህ አለቻት ከቤትሽ ደርብ ለምን አትወርጂም እህልንስ ለምን አትበይም።

፬. ከዚህም በኋላ በጨልታ ወረደች እንዳይናገርባትም በር ለሚጠብቀው የወርቅ ወልባዋን ሰጠችውና ወደ ጳውሎስ ሄደች ጳውሎስም በደስታ ተቀበላት የክብር ባለቤት የሆነ የክርስቶስንም ሃይማኖት አስተማራት በማግስቱም እናቷ በደረሰች ጊዜ ከጳውሎስ ዘንድ ተቀምጣ አገኘቻት ወደ አገረ ገዢውም መኮንን ሂዳ ክርስቲያን እንደሆነች ወነጀለቻት መኮንኑም የእርሷን ቅጣት አይተው ይፈሩ ዘንድ የአገር ልጆችን ሰብስበው ወደ እሳት እንዲወረውሯት አዘዘ ያን ጊዜም በመስቀል ምልክት አማተበችና እነርሱ



Scanned with CamScanner

ሳይወረውሯት እርሷ ወደ እሳት ራሷን ወረወረች የነካትም ነገር ሳይኖር ከእሳት መካከል ወጥታ ወደ ጳውሎስ ሄደች።

፳. ከዚህም በኋላ የራሷን ጠጉር ቆርጣ ወገቧን ታጥቃ ወደ ማርያም መግደላዊት ሄደች እጅም ነሣቻት ከእግሯም በታች ሰገደች እንዲህም አለቻት እኔ ትምህርትሽን በሰማሁ ጊዜ አመንሁ እናቴም ለመኮንኑ ወንጀልችኝና መኮንኑም ለአማልክት ሠዊ አለኝ መሠዋትን እንቢ ባልኩት ጊዜ ባሮቹን እሳትን አንድዱ ብሎ አዘዛቸው እንዳዘዛቸውም ይወረውሩኝ ዘንድ ወደኔ ቀረቡ እኔ ግን በፈቃደ ወደ እሳቱ ተወረወርኩ ከክፉ ነገር ከቶ ምንም ያገኘኝ የለም ያዩም አደነቁ በጸሎትሽም ደህና ሆንኩ ማርያም መግደላዊትም ይህ ነገር የሆነው በልብሽ ቆራጥነት ነው። እግዚአብሔርም ያዳነሽ እንዲህም የሚያምኑትን የሚፈሩትና የሚያመልኩትን ያድናቸዋልና ብላ መለሰችላት ያቺም ብላቴና የከበረች ማርያም መግደላዊትን እንዲህ አለቻት።

፳፩. የአማልክት አምላክ የፍጥረታት ሁሉ ጌታ ወደ ሆነው እግዚአብሔር ወደ አምልኮቱ እንመልሳቸው ዘንድ ወደዚች አገር ተመልሰን አንድነት እንሂድ ማርያም መግደላዊትም ያቺን ብላቴና መልካም ነው እሺ አለቻት ይህንም ብለው ወደዚያ አገር ሄዱ መኮንኑም ባያቸው ጊዜ ከፊታቸው ግርማ የተነሣ በፊቷ ሰገደ እንዲህም አላት የምትኖሪበት አገርሽ ወዴት ነው ስምሽስ ማነው የአባትሽና የእናትሽ ስም ማነው? እንዲህም ገገር መኮንኑ ተነጋገራት።

፳፪. ይቺ ማርያም መግደላዊትም ዓለምን ሁሉ በዓለምም ውስጥ ያሉትን ፍጥረታትን በፈጠረና ባዘጋጀ በፈጣሪዬ እመን ከዛሬ ጀምሮ ለረከሱና ለሚያጸይፉ ራሳቸውን እንኳን ማዳን ለማይችሉ ለአጵሎን ለአርጨምስና ለአቴና አትስገድ አለችው።



Scanned with CamScanner

፰. መኮንኑም እንዲህ አለ እነዚህማ አማልክት አማልክቶቼ ናቸው። አጵሎንም ጌታዬ ነው ለሌላ አልሰግድም አንቺ ግን እጅ እንደነሣሁሽ ለአማልክቶቼ ካልሰገድሽና ካልተገዛሽ አሰቃይሻለሁ።

፱. እርሷም አብረዋት ያሉትን ሌሎች ደናግል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የበረታን እንሁን ይህም መኮንን በአለቆቹ ፊት ያፈረ ይሆናል አለቻቸው ምክሯን ሰምተው በመንፈስ ቅዱስ የጸኑ ሆኑ። ይህም መኮንን ያሉትን ሰምቶ አገልጋዮቹን በመስቀል ላይ ሰቅለው ያሰቃዩአቸው ዘንድ አዘዘ ለጣዖት መስገድን እንቢ ብለዋልና።

፲. እነዚህም አገልጋዮችና ጃንደረቦች እንዲህ አሉ ለእኛስ እነርሱን ሰቅለን ማሰቃየት አይገባንም እነርሱም እግዚአብሔር የሚወዳቸው እነርሱም የሚወዱት ወዳጆቹ ናቸውና እርሱም ለወዳጆቹ ሁሉ መልካም ነገርን የሚያደርግ ነውና እኛም እነርሱ በሚያመልኩት አምላክ ሰማይና ምድርን ባሕሩን ወንዞችንና የውሃ ምንጮችን በዓለም ውስጥ ያለውን ሁሉ እኛንም በፈጠረ አምላክ እኛ እናምንበታለን ይህንንም ብለው ወደእሊያ ደናግል ሸሹ ሰገዱላቸውም እንዲህም አሏቸው። ዕድል ፈንታችን ከእናንተ ጋር ይሁን ፍለጋችሁንም እንከተላለን የዚያንም መኮንን ትእዛዝ እንቢ ብለናል።

፲፩. ማርያም መግደላዊትም እነዚያን የንጉሥ አገልጋዮች ተስፋ ከመቁረጥ የከፋ ኃጢአት የለምና ተስፋ የምትቆርጡና ወላዋዮች አትሁኑ አለቻቸው። እኔም መጽሐፍ ያለውን ሰምቻለሁ ሰው ሕጌን ከጠበቀ በእግዚአብሔር ፊት እንደመላእክት ይሆናል የሚል ነው።

፲፪. ይህንንም ብላ ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ስትል ጸለየች ወገኖችህ ወደ ተራራዎች ቢሰደዱ በበረሃዎችም ውስጥ ቢመላለሱ እንደ ዐይን ብሌን አንተ ጠብቀሃቸዋልና



Scanned with CamScanner

እንደነርሱ አጽንተህ ጠብቀን ለነግህ የማያሳድሩ አንበሳና ተኩላ ነጣጥቀው እንዳይበሉን አንተ አትጣለን፡፡

፲፫. ወደአንተ የተመለሱ እነዚህ ባሮችህን መዘባበቻ አታድርጋቸው አቤቱ ጸሎቱን ስማኝ ኃጢአተኛ ሰው ከሚያመጣው ስቃይ አድነኝ ከክፉዎች ምክርም እንደበታቸውን እንደ እባብ ካሰሉ ከአመጸኞች ብዛትም አድነኝ የአቤልን መሥዋዕት የአሮንንም ዕጣን እንደተቀበልክ ልመናዬን ተቀበለኝ እንደዚህም በብዙ ቋንቋ አብዝታ ጸለየች፡፡ ጩኸቷም በእግዚአብሔር ፊት ተሰማ እንዲህም አላት አትፍሪ አትደንግጭም የዚህ መኮንን አማልክት በአደባባይ እንዳለ ጭቃ ይሆናሉ እንደ ዕፀ ከንቱም በፊትሽ የወደቁና የተጣሉ ይሆናሉ፡፡ እርሱም ከአማልክቱ ጋር ያፈረ ይሆናል፡፡ ይህንንም በሰማች ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገነች፡፡

፲፬. ዳግመኛም እንዲህ ሲል ወደርሷ መልእክተኞችን ላከ እኔ አክብሬ እጅ ነስቼ ተቀበልሁሽ እንግዲህ ወዴት ትሄጃለሽ ከእጄ የምታመልጪ አይመሰልሽ ብታስቢም የምታመልጪ አይምሰልሽ የፈለግሁትን በአንቺ ላይ አደርጋለሁ ማምለጥ አይቻልም ያንንም መልእክተኛ እንዲህ አለችው፡፡ እኔ በእግዚአብሔር ታምኛለሁ የሚያስፈራኝ ምንድን ነው የሚያስደነግጠኝስ ማነው? እርሱም የሚያድን መታመኛዬ ነው ይህንንም ብላ ሰማይና ምድርን ወደፈጠረ አምላክ ጸሎትን ዳግመኛ ጸለየች ወገቧንም ታጠቀች ማቅንም ለበሰች በጾም በጸሎት በስግደት እግዚአብሔርን ማገልገል ጀመረች፡፡

፲፭. አገልጋዮቿም እግዚአብሔርን የሚፈሩትና የሚያመልኩት ትዕዛዙንም የሚያደርጉ ወገባቸውን በወርቅ መታጠቂያ የታጠቁ ያማሩ ልብሶችን የለበሱ ሁነው ሁል ጊዜ በጸሎት የተጠመዱ እስከ ዘጠኝ ሰዓትም እየዋሉ ከድሆችና

ከምስኪኖች ጋር በአንድነት እህልን የሚመገቡ ሆነ የእግዚአብሔር ጸጋ አድሮባቸው ፈጽሞ ደስ ብሏቸው በጎ መሥራትን ጨመሩ ይቺም የተመረጠችና የከበረች ጽኑ ተጋድሎን እያበዛች ሄደች፡፡

፲፩. ከዚህም በኋላ ትዕቢተኛው መኮንን ላከ እንዲህም አለ እነዚያን ባሮች አምጧቸው ከእጄ የሚድናቸው የለምና እኔም እቀጣቸዋለሁ፡፡ ይህንንም ሰምተው ለማርያም መግደላዊት ነገሯት እርሷም ይህን ሰምታ በእኔ ላይ የሚያደርገውን አይ ዘንድ እኔ ብቻዬን እሄዳለሁ እናንተም ዜናዬን ሰምታችሁ ትመጣላችሁ እነርሱም አገልጋዮች እንደሌሉሽ ብቻሽን ሁነሽ ትሄጃለሽን አሏት፡፡

፲፪. እርሷም እንዲህ አለቻቸው ነገሬን ስሙ ቃሌንም አድምጡ ይሄ መከራ ፈቃደ ነው የምትሰሙኝም ከሆነ እኔ ከእናንተ አልለይም ይህንንም ብላ በላያቸው አማተበች እርሷም ብቻዋን ሄዳ ትዕቢተኛና ተሳላቂ በሆነ በዚያ መኮንን በፊቱ ቆመች፡፡

፲፫. ትዕቢተኛውን መኮንን ሰላም እልሃለሁ አለችው እርሱም ይህ ነገርሽ ዘለፋ ነው፡፡ ነገር ግን አማካሪዎችሽ የሆኑ ወንዶችና ሴቶች ባሮችሽ ወዴት አሉ አላት፡፡ እርሷም እንዲህ አለችው መታመኛዬ እግዚአብሔር ነውና ሕይወት ለሌላቸው አማልክትህ እኔ ብቻዬን እበቃቸዋለሁ፡፡

፲፬. ይህንንም የዘለፋ ቃል ሰምቶ ልብሶቹን ቀደደ ራሱንም አከከ አገልጋዮቹንም ኑ ወደ አማልክቶቻችን እንሂድ አላቸው፡፡ እነርሱም ይህንን ሰምተው ወደ አማልክቶቻቸው ሄዱ በደረሱ ጊዜም እንደ ደቀቀ ሸንበቆ ሁነው አገኟቸውና ታላቅ ኃዘንን አዘኑ ከመኮንኑም ጋር አፈሩ ይቺም የተመረጠችና የከበረች ብላቴና ጤቅላ ስለድንቁርናቸው ታዝን ነበር እነርሱም በሁለተኛው ቀን ስብሰባ አድርገው እንዲህ ሲሉ ጥሩ ምክርን መከሩ ወደዚህች የሕይወት

ሙሽሪት እንመለስና እርሷ ባመነችው አምላኳ እንመን ይህንንም ብለው ለሰማይና ለምድር ንጉሥም ተገዙ እርሷም ወደወገኖቿ ተመለሰች እነርሱም የዘገየሽው በደህና ነውን እኛ በመዘግየትሽ ደነገጥን አሏት እርሷም እኔስ በደህና አለሁ እናንተ አገልጋዮች ግን የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሁኑ ያ መኮንንም ከወገኖቹ ጋር አመነ እግዚአብሔርም በቸርነቱ ብዛት ወደአምልኮቱ መልሷቸዋልና አምላካቸው የነበረው አጽሎንም ያፈረና ተቀጥቅጦ የደቀቀ ሆነ ሲያመልኩት የነበሩ እነርሱም እንደኩስና እንደ እሬት እንደ አደፍ ጨርቅም አደረጉት ወደ ንስሐም ተመለሱ፡፡

፳. አሁንም ኑ ወደ አገራቸው እንሂድ ከዚያም ጌታ እስኪያስነሳንና ወደሌላ አገር እስከምንሄድ ድረስ አብረናቸው እንቀመጥ አለቻቸው፡፡ እነርሱም ወደርሳቸው መሄዳችን መልካም ነው እንሂድ አሏት፡፡ ይህንንም ብለው ወደዚያ አገር ተመልሰው በሰላም በፍቅር ገቡ እርስበርሳቸውም ሰላምታን ተለዋወጡ የአገር ሰዎችም እኛ የአጽሎንን ሃይማኖት ክደናልና እንጠመቅ ዘንድ እንሻለን አሉ፡፡ ከዚህም በኋላ የክብር ባለቤት በሆነ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምነው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠመቁ ሕይወትንም በወለደች በእመቤታችን ድንግል ማርያም ጌቶቻችን በሆኑ ሐዋርያትም በስማቸው በከበረች ማርያም መግደላዊትም ስም አብያተ ክርስቲያናትን አነጹ በጌጥ ሁሉ አስጌጧቸው ሸለሟቸውም የግምጃ ልብሶችንም የወርቅ ጻሕሎችንና ጽዋዎችን አዘጋጅተው አነዚያን አብያተ ክርስቲያናት አከበሯቸው፡፡

፳፩. በዚያችም አገር ፈጽሞ ታላቅ ደስታ ሆነ ዕውራንም ብርሃንን አግኝተዋልና ሐንካሶችም ተስተካክለዋልና ለምጻሞችም ነጽተዋልና ንጉሡም በሃይማኖት የጸና



Scanned with CamScanner

የተስተካከለ ሆነ ሕዝቡም መኳንንቱም በፍርሃት ሆነው ለእግዚአብሔር ተገዙ፡፡

፭፪. ከዚህም በኋላ አንድ ጋኔን የያዘውን ሰው ወደ ቅድስት ማርያም መግደላዊት አመጡት በአያትም ጊዜ ሸሸ፡፡ ይዘውም በሰንሰለት አጽንተው አሥረው በፊቷ አቆሙት እንደ ሜዳ አህያ ተንከባለለ እርሷም የክብር ባለቤት በሆነ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ወጥተህ ወደ አገርህና ወደ ባልንጀሮችህ ሂድ አለችው ያን ጊዜ ግንድ መስሎ ከሰውየው ወጥቶ ለባልንጀሮቼ መሳለቂያ መዘባበቻ ሆኛለሁና ወዮልኝ አለ፡፡ የእግዚአብሔርን ስም ለሚጠሩ ሁሉ ከደይን በታች ምንጣፍ ያደርጉኛልና፡፡

፭፫. የከበረች ማርያም መግደላዊትም ስምህ ማነው አገርህስ ወዴት ነው አለችው እርሱም እንዲህ ብሎ መለሰላት ስሜ መስሕት ነው ኑሮዬም ከአጵሎን ከፊውና ከፍውዝ ጋር አምላክን እየተመሰልን ሰዎችን እያሳትን እየበላንና እየጠጣን ነው፡፡ የፍጥረቱ ሁሉ መሳሳቻ የሆነ በጉባኤ ሁሉ መካከል እንዲህ ተናገረ፡፡

፭፬. ራሱን እንኳን ማዳን የማይችል ለእኛ አምላክን ይመስለን ነበር ብለው ሕዝቡ አደነቁ እግዚአብሔርን እንዲህ እያሉ አመሰገኑት ለእኛ ለሁላችን መዳኛ ሰጥቶ ወገኖቹን ያዳነ ሰማይና ምድርን የፈጠረ እግዚአብሔር ፈጽሞ የተመሰገነ ነው፡፡ ይህንንም ካሉ በኋላ ፍጹም ደስታን በማድረግ በእግዚአብሔር ቤቶች ውስጥ በደስታ ዘመሩ የከበረች ማርያም መግደላዊትም በዚያች ሀገር ሶስት ዓመት ኖረች በዱር ከለመለመ ቅጠል በቀር እህልም አልበላችም ከዚህም በኋላ የሀገር ሰዎችን እንዲህ አለቻቸው እኔ ወደ ሌላ መኖሪያ እሄዳለሁ፡፡ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን የሕይወትን መንገድ ይምራችሁ ከሐሰተኛ ጠላትም ያድናችሁ የረከሱ አጋንንትም ከእናንተ ይራቁ፡፡



Scanned with CamScanner

፳፰. የነቢያት የሐዋርያት በረከት የጻድቃን የሰማዕታትም በረከት የትጉሃን መላእክት በረከትም በላያችሁ ይደር አምላክን የወለደች የቅድስት ድንግል እመቤታችን ማርያም በረከቷ ይደርባችሁ የብልሆች ደናግል በረከትም ይደርባችሁ በፍቅር በሰላም ጸንታችሁ ኑሩ ያለፍቅር መጠቀም የለም ከሥጋችሁ ቆርጣችሁ ብታበሉ ከደማችሁ ቀድታችሁ ብታጠጡ ያለዕረፍትም ብትጸልዩ ጥሪታችሁን ሁሉ ብትሰጡ ያለ ፍቅር ከንቱ ነው:: እግዚአብሔር ከመሥዋዕት ይልቅ ምጽዋትን እመርጣለሁ ብሏልና::

፳፱. ቅዱስ ጳውሎስም አለ የሰውን ሁሉ ቋንቋ ባውቅ በመላእክትም ሁሉ ቋንቋ ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮህ የነሐስ መረዋ ሆንኩ ተራራ እስከ ማፍለስ የሚደርስ ፍጹም ሃይማኖት ቢኖረኝ ፍቅር ከሌለኝ ከንቱ ሆንኩ እንዲሁም መከራቸውና አስተምራቸው አምላክ ወዳዘዛት ቦታ ተጓዘች:: በጸሎቷ የሚገኝ በረከቷ ከእኛ ጋር ከወንዶችና ከሴቶች አገልጋዮቿ ጋር ይሁን ያለምርመራም ወደደብረ ጽዮን ታስገባን ለዘላለሙ አሜን::

# ምዕራፍ አሥራ ስድስት

# አንደኛ ተአምር

፩. በረከቷ በእኛ ላይ ይደርብንና ለዘላለሙ ከእናቷ ማሕፀን በእግዚአብሔር ዘንድ የተመረጠች በሐዋርያትም የከበረች ከእርሳቸው ዘንድ ዲያቆናዊት ተብላ የዲቁና ክህነትን ተሾማለችና እናታችን ቅድስት ማርያም መግደላዊት ያደረገችው ተአምር ይህ ነው::

፪. የክርስቲያን ወገኖች ሆይ እንነግራችሁ ዘንድ በዕዝነ ልቡና ስሙ በትሩፋቷ በአገልግሎቷ እግዚአብሔርን ደስ የምታሰኝ ትሕትናዋንም በአዩ ጊዜ እንዲህም ስታገለግል በጠባይም

ሆነ በትሩፋት ሥራ እንደርሷ ያለ እንደሌለ አይተው እርሷም ተከትላቸው ስታገለግል እነርሱ ዲያቆናዊት ብለው እንደሾሟት።

፫. በአዳራሽም ውስጥ ሳለች ጸዓዳ ርግብ መጥቶ ይጋርዳታል እርሱም መንፈስ ቅዱስ ነው።

፬. በእሳት ሠረገላም ተጭና ትሄዳለች። ዳግመኛም በአንበሳ ላይ ትጫናለች። ከእርሱ ጋር ስትጫወት እጆቹን እግሮቹን አስራ በአጠገቧ ታስቀምጠዋለች። ሐዋርያትም ሥራዋን አይተው ያደንቃሉ እርሷ በአንበሳ ጀርባ ተቀምጣ የምትጓዝ ሁና እንደ ፈረስ ታስረዋለች። ከእርሱ ጋር መጓዝ ትወድ ነበርና ከተአምራቷና ከገድሏ ማማር የተነሣ ያደንቁ ነበር።

፭. እርሷም የዲቁና ክህነትን የተሾመች ናት። ይህም የክህነት ሹመት ሴቶችን ለማስተማር ነው። እርሷ በአገልግሎቷ ሰውንና እግዚአብሔርን ደስ ታሰኛለችና።

፮. በትሩፋቷ የተሰጣት የክህነት ሹመት እንደ ክህነት ሥርዓት ሁሉ ቅዱስ ምሥጢር መሥዋዕትን አዘጋጅቶ ወደ መንበር ለማቅረብ አይደለም።

፯. በአንዲት ዕለትም ወደ ሐዋርያት በመንገድ ውስጥ ስትጓዝ የሞተ አንበሳ አየች እርሷም ከተጫነችበት አንበሳ ላይ ወርዳ እንዲህ አለችው። አንተ ቁጡ ወደ ሞተው ተመልከተ ከባልንጀሮችህና ከወገኖችህ የሆነ የሞተ ይመስላል።

፰. መልክተኛው አንበሳም ወደእሱ ሄደ። ሙቶም አገኘው። ወደእሷም ተመልሶ አዎን ሙቷል የገደለውን ግን አላወቅሁም አላት።



Scanned with CamScanner

፱. እርሷም እንዲህ አለችው አንበሳ ሆይ ሒድ እንዲህ ስትል ጥራው የክብር ባለቤት በሆነ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ተነሥ ትልሃለች የእግዚአብሔር ባርያ ማርያም መግደላዊት በለው ያ አንበሳም እንደ ሰው ተናግሮ እንዲህ ብሎ ጠራው ወንድሜ አንተን አናግርሃለሁ የግሩማን አናብስት ልጅ የእግዚአብሔር አገልጋይ ትጠራሃለችና ከተኛህበት ተነሥተህ ወደ እርሷ ሒድ እልሃለሁ አለው።

፲. የተኛ ሰው ከተኛበት እንደሚነሣ ወዲያውኑ ተነሥቶ የእግዚአብሔር አገልጋይ ወደሆነች ማርያም መግደላዊት ሔዶ ሰገደላት ለንግሷም ተገዢ ሆነ። አስቀድሞ ከእርሷ ዘንድ ይኖር ከነበረው አንበሳ ጋርም አንድ ሆነው በኋላዋ የሚከተሏት ሆኑ ብንሞትም ታነሣናለች አሉ እንዲሁም እኛን ከኃጢአት ሞት ታንሣን።

፲፩. ወንድ ባሪያ ለጌታው ሴት ባሪያ ለእመቤቷ እንደሚያገለግሉ በቀንም በሌሊትም እያገለገሉ ኖሩ።

፲፪. እርሷም ከእነርሱ በሞት እስከተለየች ድረስ ሐዋርያትን እያገለገለቻቸው ኖረች።

፲፫. የክርስቲያን ወገኖች እስኪ አስተውሉ የክብር ባለቤት ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዚች ለከበረች ማርያም መግደላዊት አብዝቶ ጸጋውን እንደሰጣት ሰውንም አብዝቶ በመውደድ መታሰቢያዋን የሚያደርጉ ስሟንም የሚጠሩትን ቤተክርስቲያን በስሟ የሚሠሩትን ዕድል ፈንታቸውን ከተመረጡ ባለሟሎቹ ጋር ሲኖር እርሷን ለሰው ልጆች ድኅነት ምክንያት እንዳደረጋት እዩ።

፲፬. እንዲሁ እኛን የክርስቲያን ወገኖች አገልጋዮቿን ታድለን ለዘላለሙ አሜን።



Scanned with CamScanner

# ሁለተኛ ተአምር

፩. በጸሎቷ የሚገኝ በረከቷ በዕውነት ለዘላለሙ ከእኛ ጋር ይኑርና የከበረች ማርያም መግደላዊት ያደረገችው ተአምር ይህ ነው።

፪. በቅድስት ማርያም መግደላዊት ቤተ ክርስቲያን አካባቢ የምትኖር የዕለት ራት የሌላት አንዲት መበለት ደኃ ሴት ነበረች።

፫. እርሷም ወደ ቤተክርስቲያንዋ ሔዳ ጸለየች። ዕንባዋም እንደ ውኃ ይፈስ ነበር። እንዲህም አለች። እመቤቴ ንግሥት ሆይ እኔ የደከምኩ ደኃ ነኝ ምግብን የሚሰጡኝ ልጆች የሉኝም። እኔም ከበጎ ሥራ ሁሉ መስጠት ይሻላል የሚል ከመጽሐፍ ቃል ሰምቻለሁ በማርያም መግደላዊት አዳራሽ ውስጥም እንዲህ ጸለየች ይህንም ብላ በምሰሶው ጎን አሸለበች።

፬. ከዚህም በኋላ በሕልም እንዲህ ስትል ተናገረቻት ሴትዮ ለሥጋ ስለሚሆን ምግብ ለምን ትጨነቂያለሽ ከሁሉም የሚያስጨንቅ የነፍስ ምግብና ልብስ ነው እንጂ

፭. ዳሩ ግን የቁርባኑ ሥርዐትና የቅዳሴው ጸሎት ከተፈጸመ በኋላ ፈጥነሽ ወደ መኖሪያሽ ሂጂ።

፮. ከእንቅልፏም በነቃች ጊዜ የተመኘችውን ስለ አገኘች ደስ አላት የቅዳሴውም ጸሎት ከተፈጸመ በኋላ ወደ መኖሪያዋ ሄደች ብዙ የሆነ የወርቅ ልጥርን አግኝታ ደስ አላት እጅግም አደነቀች ለብዙ ገንዘብም ሸጠችውና ባለጸጋ ሆነች ብልጽግናዋም የማይሰፈር የማያልቅ ሆነ።

፯. እርሷም እስከ ዐረፈችና በማርያም መግደላዊት ጸሎት ወደ ሰማያዊ መንግሥት እስከ ገባች ድረስ በዘመኗ ሁሉ የቅድስት ማርያም መግደላዊት መታሰቢያዋን እያደረገች



Scanned with CamScanner

ኖረች። በጸሎቷ የሚገኝ በረከቷ ከእኛ ጋር ለዘላለሙ ጸንቶ ይኑር አሜን።

## ሦስተኛ ተአምር

፩. በጸሎቷ የሚገኝ በረከቷ በእኛ ላይ በዕውነት ለዘላለሙ ይደርብንና የከበረች ማርያም መግደላዊት ያደረገችው ተአምር ይህ ነው።

፪. ጌታችን ባርኮ ከሴትና ከልጅ በቀር አምስት ሺህ ሰዎችን በአጠገበበት የእንጀራ ፍርፋሪ ድንቅ ተአምራትን የምታደርግ ሆነች።

፫. በዚያ የእንጀራ ፍርፋሪ በሽተኞችን ታድናለች የዕውራን ዐይኖችንም ታበራለች በየጥቂቱ በምትሰጣቸው ጊዜ በየዓይነቱ ከሆነ ከልዩ ልዩ በሽታቸው ይድናሉ።

፬. ለምጻሞችም ይነጻሉ። አጋንንትም ይወጣሉ።

፭. ድኅንትና ረድኤትን የሆነላት ይህን የዕውነት ምግብ ትሰጣቸዋለች። ለይሁዳ አውራጃ ለጢሮስና ለሲዶናም ለሚጎራበቱ ለመግደሎ አውራጃዎችም ትይዩ ለሆኑ ሁሉ ፈዋሽ ሁኖላታልና።

፮. በቍስለ ሥጋ የታመመ አንድ ሰው ነበረ። ሥጋው ሁሉ አብጦ በክፉ አሟሟት ይሞት ዘንድ ተቃረበ።

፯. ከዚህም በኋላ ቤተሰቦቹ በዓልጋ ተሸክመው ወደ ማርያም መግደላዊት ቤት ወሰዱት። እርሷም ጌታችን ከባረከው ከቤቷ ከአለው ከዚያ እንጀራ ፍርፋሪ ሰጠችው። ያ በሽተኛም ወዲያውኑ ድኖ እንደ እንቦሳ ዘለለ። የዚያ ሰው ዘመዶቹም ደስ አላቸው። ለፍላጎቷና ለድሆችም የሚሰጥ እጅ መንሻ ሰጡ። ያ የዳነው ሰውም ሲያገለግላት ኖረ በጸሎቷ የሚገኝ በረከቷ ከእኛ ጋር ይኑር ለዘላለሙ አሜን።



Scanned with CamScanner

# አራተኛ ተአምር

፩. በጸሎቷ የሚገኝ በረከቷ ከእኛ ጋር በዕውነት ለዘላለሙ ይኑርና የከበረች ማርያም መግደላዊት ያደረገችው ተአምር ይህ ነው ለዘላለሙ አሜን።

፪. ከእስማኤል ወገን የሆነች አንዲት ብላቴና በተመረጠችና በከበረች በቅድስት ማርያም መግደላዊት ቤት አቅራቢያ የምትኖር ነበረች።

፫. በቅድስት ማርያም መግደላዊት ቤት ውስጥ የሚደረገውን ቁጥር የሌለው ታላላቅ የሆኑ ድንቆች ተአምራቶችን በአየች ጊዜ የክብር ባለቤት በሆነ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖት አመነች።

፬. ወገኖቿም ሰምተው ወደ እናትና አባቷ ሂደው ልጃችሁ በደለች በክርስቶስም አመነች አሏቸው ወላጆቿም በመረመሯት ጊዜ አዎን አመንኩ አለቻቸው እነርሱም ገረፏት በዚያን ጊዜ ሞተች።

፭. ከዚያም በኋላ ቅድስት ማርያም መግደላዊት የክብር ባለቤት ወደሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጸለየች ወዲያውኑ ያለምንም ጥፋት በጌታችን ኃይል ተነሣች።

፮. አባትና እናቷ ወገኖቿም ይህን ድንቅ ተአምር በአዩ ጊዜ የክብር ባለቤት በሆነ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ። ቅድስት ማርያም መግደላዊትንም አከበሩዋት በጸሎቷ የሚገኝ በረከቷ ከእኛ ጋር ይኑር ለዘላለሙ አሜን።

# አምስተኛ ተአምር

፩. በጸሎቷ የሚገኝ በረከቷ ከእኛ ጋር በዕውነት ይኑርና የከበረች ማርያም መግደላዊት ያደረገችው ተአምር ይህ ነው ለዘላለሙ አሜን።



Scanned with CamScanner

፪. ጽኑዕና አስጨናቂ በሆነ በሚጥል በሽታ የታመመ አንድ ሰው ነበረ ቤተሰቦቹንም ታድነኝ ዘንድ ወደ ማርያም መግደላዊት ቤት ውሰዱኝ አላቸው።
፫. በሰወሰዱትም ጊዜ ከቅድስት ማርያም መግደላዊት ቤት ከአለው የበረከት ኀብስት በመብላት ዘወትር እየጣለ ከሚያንፈራፍረው ደዌው ዳነ። ዘመዶቹና ቤተሰቦቹ ሁሉ ደስ አላቸው።
፬. እርሱም ለድሆችና ለምስኪኖች ለባልቴቶችና ለሙት ልጆች ለመጻተኞችና ለተቸገሩ ሁሉ ከገንዘቡ ብዙ ምጽዋትን ሰጠ።
፭. እኩሌታ ገንዘቡንም ለቤተ ክርስቲያን ማስጌጫና ለሚፈለገው ሥራ ሁሉ ይሆን ዘንድ ሰጠ።
፮. እንደ ዋልያም እየዘለለ ወደ ቤቱ ተመለሰ።
፯. ይህን ድንቅ ሥራ ያዩ የአገር ሰዎችም ዕልልታ አደረጉ ጸጋውን ለሰው ልጆች ለሰጠ ለጌታችንና ለመድኃኒታችን ምስጉን ቡሩክ ለሆነ ስሙ ምስጋናን አቀረቡ።
፰. ይህም ሰው ከሚስቱ ከልጆቹ ከቤተሰቦቹ ሁሉ ጋር ቤተ ክርስቲያንን እያገለገለ የከበረች ማርያም መግደላዊትንም በማክበር ጌታችንንና መድኃኒታችንን ፈጽሞ ሲያመሰግን ኖረ በጸሎቷ የሚገኝ በረከቷ ከእኛ ጋር በዕውነት ለዘላለሙ ይኑር አሜን።

## ስድስተኛ ተአምር

፩. በጸሎቷ የሚገኝ በረከቷ ከእኛ ጋር በዕውነት ይኑርና የከበረች ማርያም መግደላዊት ያደረገችው ተአምር ይህ ነው ለዘላለሙ አሜን።
፪. ሥራው ላማረ ቤተ መቅደሷ ሥንዴውን ወይኑን ዕጣኑን ዘይቱን መጋረጃውንም በመስጠት የከበረች የማርያም መግደላዊትን መታሰቢያዋን በሕይወቱ ዘመን ሁሉ የሚያደርግ አንድ ሰው ነበር።



Scanned with CamScanner

፫. እርሱም ስለ ከበረች ማርያም መግደላዊት ፍቅር ድሆችን ምስኪኖችን ባልቴቶችን ድሃ አደጎችንና መጻተኞችን እየተቀበለ ይረዳቸዋል።
፬. የዚህም ሰው የብልጽግናውም ምክንያት የሆነው በከበረችና በተመሰገነች ማርያም መግደላዊት ቤት በሚኖረው የበረከት እንጀራ ነው።
፭. መግደሎ በሚባለውም አገር ድኃና ጠም አዳሪ ምስኪን የለም። በዚያችም አገር የሚኖሩ ሁሉ በወርቅ በብር በዕንቍ የከበሩ ናቸው። ያ የበረከት እንጀራ በአገራቸው ውስጥ ሁሉ ይኖራልና ስለሚኖር ረኃብ ጥም ኀዘን ትካዜ የለም። ሕይወታቸው ሆኑአልና።
፮. ለሁሉ ሕይወትን የሚያድል ከሰማይ የወረደው ኅብስተ ሕይወት እንደሆነ። በከበረች ማርያም መግደላዊት በጸሎቷ ለሁላችንም የጥምቀት ልጆች ሕይወትን ይሁነን ለዘላለሙ አሜን።

## ሰባተኛ ተአምር

፩. በጸሎቷ የሚገኝ በረከቷ ከእኛ ጋር በዕውነት ይኑርና የከበረች ማርያም መግደላዊት ያደረገችው ተአምር ይህ ነው ለዘላለሙ አሜን።
፪. በቅድስት ማርያም መግደላዊት ቤተ ክርስቲያን የሚያገለግል አንድ ሰው ነበረ በጾና እምነትም መተሰቢያዋን ያደርጋል በጠዋትና በማታም ወደ ቤተ መቅደሷ ደጃፎች በመገሥገሥ ከእርሷ ምሕረትን ረድኤትን ተስፋ አድርጎ ችግር ላለበት ሁሉ ስለ ስሟ ከገንዘቡ ይሰጣል።
፫. ስለዚህም በልመናዋና በአማላጅነቷ ክብርን ብልጽግናን መወደድንም አገኘ።
፬. ይቺም የከበረች ማርያም መግደላዊት በእርሷ ዘንድ የሚማጸኑትን የምትረዳቸው በኤዶም ገነትም ወደ ተተከለ ድንኳን ታስገባቸው ዘንድ የምሕረት ቃል ኪዳን



Scanned with CamScanner

ተሰጥቷታል በጸሎቷ የሚገኝ በረከቷ ከእኛ ጋር ለዘላለሙ ይኑር አሜን።

## ስምንተኛ ተአምር

፩. በጸሎቷ የሚገኝ በረከቷ ከእኛ ጋር በዕውነት ይኑርና የከበረች ማርያም መግደላዊት ያደረገችው ተአምር ይህ ነው ለዘላለሙ አሜን።

፪. የዚህች የክብር የተድላ የደስታ ወንዝ የጥበብ የምክር የዕውቀት ምንጭ የሆነችዋን ቅድስናዋን ክብርዋን ልዕልናዋን እንነግራችሁ ዘንድ ወንድሞቻችን እኅቶቻችን ስሙ።

፫. ከተመረጡና ከከበሩ ደቀ መዛሙርቱ ቀድማ የመድኃኒታችንን የትንሣኤውን ምሥጢር ማየት የተገባት ሁናለችና።

፬. ለሚወዱት ያዘጋጀውን የመንግሥተ ሰማይን መክፈቻ ከተቀበሉ ባለሟልነትን ከተሞሉ ሐዋርያት ቀድማ በማየት ለእሳቸው ያልተሰጠ ቀድሞ ማየት ስለተሰጣት በሀብተ ልዕልና ፍጽምት ናት።

፭. እንደ በደላችን ሳይሆን እንደ ቸርነትህ አምላካችን ቅዱስ ምሥጢርህን ለማየት እንደእርሷ የተዘጋጀን አድርገን ጥቂት እንኳን በጎ ሥራ የሌለን ነን። ነገር ግን የምሕረትህ ማዕበል ያሥጥመን።

፮. የኃጢአታችንም ቊጥሩ ከባሕር አሸዋና ከሰማይ ከዋክብት ቢበዛ ልዕልናን ክብርን ውዳሴን በተመላች በእናታችን በቅድስት ማርያም መግደላዊት አማላጅነት ምሕረትህ በላያችን ትሠልጥን ትንገሥ በጸሎቷም የሚገኝ በረከቷ በጸሎቷ ኃይል ከተማጸን ከሁላችን ጋር በዕውነት ለዘላለሙ ይኑር አሜን።



Scanned with CamScanner


# በደብሩ የሚከበሩ ክብረ በዓላት

1. ሚያዝያ 23 የቅዱስ ጊዮርጊስ በዓለ ዕረፍት
2. ነሐሴ 6 ቀን የቅድስት ማርያም መግደላዊት በዓለ ዕረፍት
3. መስከረም 29 ቀን የቅድስት አርሴማ በዓለ ዕረፍት
4. መስከረም 21 ቀን የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በዓል
5. ህዳር 7 ቀን የቅዱስ ጊዮርጊስ ቅዳሴ ቤቱ በዓል
6. ታህሣሥ 6 ቀን የቅድስት ለርሴማ ቅዳሴ ቤቷ
7. ጥር 6 ቀን የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ግዝረትና የቅድስት ማርያም መግደላዊት በዓለ ልደት
8. ጥር 18 ቀን የቅዱስ ጊዮርጊስ ዝርወተ አጽሙ በዓል
9. ሰኔ 21 ቀን የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቅዳሴ ቤቷ
10. የካቲት 23 ቀን የቅድስት ድንግል ማርያም መግደላዊት ቅዳሴ ቤቷ እና ቅዱስ ጊዮርጊስ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችንን የረዳበት በዓል፡፡

በእነዚህ ክብረ በዓላት ላይ ተገኝታችሁ ከቦታው በረከት እንድታገኙና በተፈጥሮ ጠበሉ ተጠምቃችሁ ድህነትና ፈውስ እንድታገኙ በቤተክርስቲያን ስም ጥሪ እናስተላልፋለን፡፡

አድራሻ፡- ኮተቤ መካነ ቅዱሳን ኢያቄም ወሐና ቤተክርስቲያን ከፍ ብሎ ደህንነት ማሰልጠኛው አጠገብ፡፡

Scanned with CamScanner




ዋጋ ብር 20:00

ጂ.ቲ ማተሚያ 011 155 11 21

Scanned with CamScanner